በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 1

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡- ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

መጋቢት ፳፱ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

ጋብቻ

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ “የጋብቻ ምስጢር ባልና ሚስትን ከምድራዊነት አውጥቶ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የሚያደርሳቸውታላቅ ምስጢር ነው።” ብሎ አስተምሮናል፡፡

- **ቅዱስ ጳውሎስም በመልዕክቶቹ “ይህ ምስጢር ታላቅ ነው፣ ጋብቻ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ነው” በማለት ስለ ጋብቻ ምስጢር ገልጦልናል፡፡**

- **በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህን ትምህርት በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስናቀርብ ከፍተኛ ደስታ እየተሰማን ሲሆን ይህ ትምህርት ለእጮኛሞች፣ አዲስ ለተጋቡ ሙሽሮች፣ ወይም ትዳራቸው ጤናማ እንዲሆን ለሚሹ ሁሉ የተዘጋጀ መሆኑን ከመግለጽ ጋር ነው፡፡**

- **ይህ ትምህርት አሥራ አምስት ክፍሎች የሚኖሩት ሲሆን በተቻለ መጠን በማዋሐድ አሳጥረን ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡ ትምህርቱ በይዘቱ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ጋብቻ የምታስተምረውን አስተምህሮ ለወደፊቱም ለመጠቀም እንዲያስችል ሆኖ የማስታወሻ ነጥቦችን ጋር ያካተተ ነው፡፡**

- **በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ትምህርት ከ20 ዓመታት በላይ ለሆነ ጊዜ የተጠቀምንበት፣ በርካታ ኦርቶዶክሳውያን የታነጹበት፣ ትዳራቸውን የጠበቁበት ሲሆን አሁንም የሚማሩትና የሚጠቀሙበት ሁሉ በትዳራቸው የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጡበትና የትዳራቸውንም መልካም ውበት የሚጠብቁበት ያድርግልን፡፡**

ጋብቻ

መግቢያ

- የዛሬውን ትምህርት ለጋብቻ የሚደረግን ዝግጅት አስመልክቶ ወይም ጋብቻቸውን በመልካም መሠረት ላይ ለማቆም ለሚሹና በጋብቻ ዙሪያ የተለያዩ ጥያቄዎች ላላቸውና ምላሽ ሊሆናቸው በሚችለው ክፍል እንጀምራለን፡፡

በጋብቻ ዙሪያ በዘመናችን ችግር አለ?

- አዎ አለ፡፡ ዘራ ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ጋብቻቸውን የሚያፈርሱ አሉ፡፡
- ከዛሬ 10 ዓመት በፊት እስከ ስድስት ወር እንኳ የመቆየት እድሎች ነበሩ፡፡
- ከዛሬ ሃምሳ ዓመት በፊት ደግሞ ፍቺ በቤተ ክርስቲያን ብዙ አይሰማም ነበር፡፡ ቢኖርም እንኳ እንደ ሚያሳፍር ነገር ተቆጥሮ ሳይሰማ በምስጢር በድብቅ ሲደረግ የሚገጥም ነበር፡፡
- በዚህ ዘመን ጋብቻቸውን ለሚፈጽሙና ለፈጸሙት ሁሉ መጸለይ አለብን፡፡

የቅድመ ጋብቻ ትምህርት ወይም ምክር አስፈላጊነት

- ይህ ጉዳይ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች የቅድመ ጋብቻ ትምህርትንና ምክርን በስፋት የመስጠት አስፈላጊነት የሚጠቁም ነው፡፡
- አንዳንዶች ይህን ትምህርት ካገቡ በኋላ ወይም አጋጣሚ ሲያገኙ ብቻ የሚከታተሉ ናቸው፡፡
- ይህን የጫጉላ ሽርሽርን እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸው በመጠየቅ የሚሸፍኑት አሉ፡፡ ስለጋብቻ መጠየቅ ችግር የለውም፡፡ ነገር ግን ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ ፍቺ ለመፈጸም መነሳት ስህተት ነው፡፡ በማንነታችን አለመጣጣም፣ ትዕግስት ማጣት፣ ነገርን በዝርዝር አርዝሞ የመግለጽ አለልቺነት ቢኖርም ሁሉ በጤናማ መልክ የሚስተካከልበት መንገድ ግን የሚገኘው ከትምህርትና ምክር ነው፡፡

ጋብቻ

ምክሩን ማን ይስጠን?

- የጋብቻ አማካሪነት ከኑዛዜና መንፈሳዊ ጎዳናን ከመጠቆም ይለያል።
- ኃጢአታችንን የምንናዘዘው (Confession) ለንስሐ አባታችን ብቻ ነው። የንስሐ አባታችንም ሰምቶ መንፈሳዊ መፍትሔ ይሰጠናል።
- የሕይወትን ጎዳና ማመልከት (Spiritual Guidance) ምስጢር አይደለም። በምዕመናንም በካህናትም ተሰጥኦው ባላቸው ሁሉ ሊፈጸም ይችላል።
- ኦርቶዶክሳዊ የጋብቻ ሕይወት አማካሪነት (Marriage Counseling) ግን የሥነ መለኮት ትምህርት፣ ከአማካሪነት ትምህርት ...ጋር አጣጥሞ በከፍተኛ ደረጃ መማርና በዕውቀት የዳበረ ችሎታን ይፈልጋል።
- ክርስቲያናዊ የጋብቻ ሕይወት አማካሪነት በመደዬው ዓለም ከሚሰጠው አማካሪነት ይለያል።
- በክርስቲያናዊ (ኦርቶዶክሳዊ) አማካሪነት እግዚአብሔር፣ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ መንፈሳዊ እሴቶች የምክሩ ማዕከል ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የእግዚአብሔር በጋብቻው መኖር የማይቀሩ መሠረታዊ ሂደቶች ናቸው።
- ስለዚህ ምክሩ ሲቀርብ ለምን እንደሚሰጠን፣ ምክሩ የሚሰጥበት ግብና፣ ከግቡም ለመድረስ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶች ሁሉ መታወቅ መካተትና መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።
- ምክሩም በየመናፈሻው ሳይሆን ራሱን በቻለ ሥርዓት ባለው መንገድ አብነት ሊሆን ከሚችለው ሀገረ ስብከት አንስቶ በመላ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሚገኙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተስተካከለና የተሟላ ሥፍራ ከማዘጋጀት አንስቶ በተገቢው መንገድ መቅረብ ይኖርበታል። ይህ ከሆነ ጋብቻን በጊዜው መታደግ ያስችላል።

ጋብቻ

የቅዱስ ጋብቻ (የፍቅር) ምስጢርነት

- ክርስቲያኖች ዘወትር ጌታችንን የምንመለከት፣ የምንሰማውና ከእርሱም የምንማር መሆን ይጠበቅብናል። በክርስቲያናዊ ጋብቻ እንዴት ማፍቀርና መኖር እንዳለብን ማወቅ የተጋቢዎች ሁሉ ግዴታ ነው።
- ወደ ጌታችን እንመልከት፣ እንዴት መኖር እንዳለብንም ከእርሱ እንስማ፣ ጠባያችንም ምን መሆን እንዳለበት ከእርሱ እንማር። "ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ።" ብሎናልና የሕይወታችን ማዕከሉ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ***ማቴ 11:29።***
- ከሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ታላቁ ምስጢር ተብሎ የተጠቀሰው የጋብቻ ምስጢር ነው።
- "ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።" **ኤፌ** 5፡30-32።
- ይህ ምስጢር ፈጽመን የማንተነትነው የማንመረምረው ታላቅ ምስጢር ነው። ተጋቢ እጮኛሞቹ ከመጋባታቸው በፊት የክርስቶስ አካል ብልቶች ናቸው። ከተጋቡ በኋላ ደግሞ አንድ አካል ሆነው የክርስቶስ አካል ብልቶች ሆነው ይቀጥላሉ። ወንዱ ክርስቶስን ሰትዋ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ይመስላሉ። ቤተ ክርስቲያንም የክርስቶስ አካል ናት።
- እግዚአብሔር አባትና እናትን ትተን በምስጢረ ጋብቻ እንዴት አንድ ስለመሆን አስተምሮናል።

ጋብቻ

የቅዱስ ጋብቻ (የፍቅር) ምስጢርነት...

- ይህም ዘፍጥ 2፡24፣ ማቴ 19፡5-6፣ ማር 10፡6-7፣ ኤፌ 5፡30-32 ተጠቅሷል፡፡

- የባልና ሚስትን አንድነት ለመረዳት የቤተ ክርስቲያንንና የክርስቶስን አንድነት መረዳት ያስፈልጋል፡፡

- ባልና ሚስቶች በግኑኝነታችን፣ በመቀራረባችን ዘወትር በየደቂቃው በየሰዓቱ እግዚአብሔር የአንድነትን ሥራ የሚሠራበት ምስጢር የጋብቻ ምስጢር ነው፡፡

- ይህ ምስጢር ለጊዜው በቦታ በመለያየት የተነሳ መንፈስ ቅዱስ የሚሰራው ሥራ የማይከፈልበት ያለ ማቋረጥ የሚቀጥል ምስጢር ነው፡፡

- ታዲያ ይህ ምስጢር ዝግጅት ያስፈልገዋል፡፡

- ለቅዱስ ቁርባን የምንዘጋጀው እንዴት ነው? ንስሐ በመግባት፡፡

ጋብቻ

የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች

- የምናደርገው ዝግጅት ምንድር ነው? ተክሊል የምናደርግበትን ቤ/ክ መምረጥ፣ ድግሱ፣ አዳራሹ፣ የጫጉላ ሽርሽር ቦታው፣ መኖሪያ ቤታችን ዌወም ሠፈራችን፣... ነው? ሰዎች በጋብቻ ዝግጅት ብዙውን ጊዜ የምናጠፋው በዚህ ነው።
- ብንተጫጭም በታወረ የፍቅር ስሜት መነዳት ብዙዎቻችን ጋር ይኖራል። ዝግጅት ብለን የምናስበው ከላይ ከተቀሱት ጥቂቶች ተጫማሪ ቢኖር ፍቅር፣ ፍቅር፣ ፍቅር... የስሜት ፍቅር ነው። የትዳሩ ዕድሜ ማጠር፣ ትዳርን በንትርኩ ወይም መጥፎ በሆነው ገጽታ የመስበኩ ሕይወት ምንጩ የዝግጅት ማነስ ነው።
- በርካታዎች ከጋብቻ ወይም ከሠርግ በፊትና በኋላ ያለው ሕይወት የተለያየ እንደሆነ ከቀደሙት አይማሩም። ገብተውበት ከወር ባነሰ ጊዜ ወደ ንስሐ አባቶቻቸው በመሄድ ያገባሁት/ያገባኋት እርሱ/ሷ አይደለም/ለችም፤ ይመልከቱ ከበፊቱ የተለየ/የች ነው/ናት ብለው እስኪጮሁ ድረስ አምነው አይዘጋጁም።
- ሰባት ሰዓት አብራችሁ ቁጭ ብላችሁ በመታገስ የምታወሩ ባለትዳሮች አላችሁ? የማትችሉም አላችሁ። ነገር ግን ለምን? ከማግባት በፊት እንዲህ ነበርን? ጠባያችንስ እንደልቡ እንዲለዋወጥ ስሜትስ እንዲገዛንና እንዲመራን ስለምን ሆንን?

ጋብቻ

የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች...

- ተጋቢዎች በትዳር ሕይወታችን፣ በገንዘባችን፣ በትምህርት፣ በማኅበራዊ ሕይወታችን፣ በልጆቻችንና በአስተዳደጋቸው ፣ አብሮን እንዲኖር በምንፈቅድለት ዘመድ ወይም ወዳጅ፣ ፈቃዳችንን በምንፈጽምበት ሁኔታ ሁሉና ወዘተ ... ሥርዓትና አቅጣጫ ሊኖረን ይገባል።
- ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያናዊ ጋብቻን፣ መተጫጨትን፣ ትዳርን ፣ ፍቺን፣ የልጆች አስተዳደግን አስመልክቶ በቤተ ክርስቲያናችን የሚገኘውን ትምህርት በአግባብ መረዳት አለብን።
- በትዳር ሕይወት ቤቱ የሚመራው በማነው? **የእያንዳንዱስ ድርሻ ምንድር ነው?... ይህን አስመልክቶ የተለያዩ ክርክሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ግን እግዚአብሔር የሚለውን እንነግራችኋለን።**
- **ለጋብቻ ሕይወት ትልቁ ትምህርት ቤት ኦርቶዶክሳዊ ወላጅ ራሱ ነው። አዲስ ተጋቢዎች ወላጆቹ ምን ያህል በሕይወታቸው ክርስቶስን እንደሚመስሉ በመመርመር ልጁ/ልጅቱ ለትዳር ያላቸውን ብቃት መገምገም ይችላሉ። የሚመረመረው የወላጆቻቸው ሀብት ቁሳቁስ አይደለም ሕይወታቸው እንጂ። ወላጆችስ የኛ በትዳር ተስተካክሎ አለመኖር የልጆቻችን የጋብቻ ሕይወት መሰናክል ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን?**
- **መልካም ወላጆችን መርምሮ ለማወቅ የንስሐ አባቶችን ጠይቁ። ልጆቻቸውን ስለሚያውቁ ይነግሯችኋል።**

ጋብቻ

የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች...

ከመተጫችት በፊት

- ሴቲቱ ነቅዕ እንደ ሌለበት ጎብስት ወንዱ ብልሽት እንዳልነካው ወይን ሆነው በቤተ ክርስቲያን የአምላካቸውን ፈቃድ እያወቁና እያደረጉ በንጽሕና መቆየት ይኖርባቸዋል።
- ልጅ ከመወለዱ በፊት አሳብ እንደሚወለድ ሁሉ ሐሳቡ ከንጽሕና ጋር ራሱን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠ ክርስቶስን እየመሰሉ ይቆያሉ።

መተጫጨት

- መንፈሳዊ፣ ልቦናዊ፣ አካላዊ፣ ስሜታዊ ብስለትን በመመርመር መወሰን።

ቅዱስ ጋብቻ (ምስጢረ ተክሊል)

- ጋብቻ ተጋቢዎቹ የሚንከባከቡት ከመተጫጨት በፊት አስበው፣ በመተጫጨት ጸንሰው ምስጢረ ተክሊል በተፈጸመበት ዕለት የሚወልዱት የመጀመሪያ ልጅ ነው።
- በሥጋ የሚወለድ ልጅ እንክብካቤ እንደሚያስፈልገው ይህ ምስጢረ ተክሊል በተፈጸመበት ዕለት የተወለደው ልጅ - ጋብቻ እንክብካቤ ያስፈልገዋል።
- በሥጋ የሚወለድ ልጅ በሽታ እንደሚያጋጥመው ይህ ምስጢረ ተክሊል በተፈጸመበት ዕለት የተወለደው ልጅ - ጋብቻ የተጋቢዎቹን ግኑኝነት የሚያበላሹ በሽታዎች ይገትሙታልና መተከምና መዳን ያስፈልገዋል። ሲታመምም ሊያክሙት የሚችሉ በርካታ ሐኪሞች አሉ፡- የንስሐ አባት፣ ኦርቶዶክሳውያን መካሪዎች... የትዳር ጤንነቱ ይመለስ ዘንድ እግዚአብሔር ያስችላቸዋል።

ጋብቻ

የጋብቻ ዝግጅት ቅደም ተከተሎች... ቅዱስ ጋብቻ (ምስጢረ ተክሊል)...

- ልጅ እጹ አንገቱ ቢታመም እጹ አንገቱ ይቆረጥ እንደማንለው ሁሉ ጋብቻም መመቆረት ይፍረስ ማለት አይገባም ማሳከም እንጂ።
- ጋብቻ በጤንነት ለመኖር ርኅራኄን፣ ወዳጅነትን፣ የጋብቻውን ፍላጎት መሟላት ይሻል።
- በክርስቶስ አንድ የሆኑትን ሊለይ የሚፈልገው ሰይጣን ነው። ሰይጣን ትዳሩን ለማፍረስ የተቻለውን ብልጠት ሁሉ ይጠቀማል። ስለዚህ ዘወትር ጌታችንን የምንመለከት፣ የምንሰማውና ከርሱም የምንማር እንሁን። ይህም ትምህርት ካማግባት አስቀድሞም ሆነ ካገቡ በኋላ ስለጋብቻ ጠንቅቆ አውቆ የጋብቻን ሕሐሐወት መንከባከብ ነው።
- ብዙዎች ይህን ትምህርት ላለመማር በአእምሮአቸው ባደረ ሰይጣን አደፋፋሪነት ዋወም በኩራት ምክንያት ያበዛሉ ትምህርቶችንና ምክሮችንም ይንቃሉ። እንዲህም እየኖሩ በቤተ ክርስቲተተን አግብተው በፍርድ ቤት ተፋተው ከፈቱ ከወራት ዋወም ዓመታት በኋላ ከተደበቁበት ወጥተው መፍታታቸውን ለንስሐ አባታቸው በመንገር ለታላቁ ምስጢር ለጋብቻ እንቅፋት ያኖራሉ።
- በ1ኛ ቆሮ 11፡18-34 ለቅዱስ ቁርባን የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት ይነግረንና ለጋብቻም የሚያስፈልገውን ዝግጅት እንድናውቅ ያሳስበናል። “ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን።”
- ሳሰሰገባቸው የሚቆርቡት የምስጢሩ ምንነት ያልገባቸው፣ አምልኮተ ቤተ ክርስቲያንን የማይፈጽሙ ዝግጅትና መርሐ ግብር የሌላቸው ናቸው። ታዲያ እነዚህ ፍርድን ይቀበላሉ። በራሳቸው ቢፈርዱ ንስሐ ገብተው ቀኖናቸው (ቅጣታቸውን) ቢፈጽሙና ቢስተካከሉ ከፍርድ ያመልጡ ነበር።
- በጋብቻም ጌታቸውን በቤታቸው የማይቀበሉ፣ በመካከላቸውም ይሆን ዘንድ የማይፈቅዱ የማመመውቁትም አሉ።

ጋብቻ

የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች

- ጋብቻ የተመሠረተው በኤደን ገነት ሲሆን በሐዲስ ኪዳንም በቃና ዘገሊላ መልሶ እንደባረከውና እንዳደሰው ከበደል በፊት ወደነበረበት ሁኔታ እንደመለሰው ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ቅዱስ አውግስጢኖስ ገልጠዋል። ***ዘፍጥ 2:18-25፣ ዮሐ 2:1-11።***
- በቃና ዘገሊላ ውሃው ወደዌወን ከመለወጡ በፊት የነበረው ስሜታዊ ፍቅርን ሲመስል ከተለወጠ በኋላ ያለው ደግሞ በመሥዋዕትነት ላለለ የተመሠረተውን ፍቅር ይመስላል።
- ክርስቲያናዊ ጋብቻ በመሥዋዕትነት ላለለ የተመሠረተ ነው። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ የተባለውም ለዚሁ ነው። ***ኤፌ 5:25።***
- የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች መተው፣ አንድ መሆንና መረዳዳት ናቸው። ***ዘፍጥ 2:24-25፣ ማቴ 19:3-12፣ ማር 10:2-12፣ ኤፌ 5:31***

– ልጆቻችን በጋብቻ ሕይወት አባትና እናታቸውን እንዲተው የምንፈቅደው መቼ ነው? ከ18 ዓመት ጀምሮ ነው።

– ድንገት በሚያገቡበት ቀን ውጡ አንበላቸው። በስሜት እንዲበስሉ በቂ ዝግጅትም እንዲኖራቸው እናድርጋቸው።

– ትተውናል ማለት አያከብሩንም ማለት ኤአደለም። ግን መውጣት ያስፈልጋቸዋል። ካልተው ወደፊት አንድ ወደ ሚያደርገው ጋብቻ ከዚያም ወደ መረዳዳት ሊደርሱ አይችሉም።

– ከ18 ዓመት ዕድሜያቸው በፊት ስሜታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ፍትወታዊ፣ የመግባባት፣ ወዘተ ምሳሌነታችንን እናሳያቸው። ከ18 እስከ 25/30 ዓመታቸው ድረስ በደንብ እንዲጸኑ እናድርጋቸው። እነርሱም በኋላ ተንከባከቡ ሲባሉ ኤአከብዳቸውምና። ዝግጅቱ ካለ ይደሰታሉ።

– ሰው አባትና እናቱን በመተው ከሚስቱ ጋር አንድ የሚሆነው በፍቅር ነው።

– የመጀመሪያው አፍቃሪ ጌታችን መድኃኔዓለም እንደሆነ ሁሉ በጋብቻም ለፍቅር መቅደም ያለበት ባል ነው። ሚስትም ከባልዋ የተቀበለችውን መልሳ ለባልዋ ትሰጠዋለች። ***1ኛ ቆሮ 7:3።***

ጋብቻ

የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች

1. መተው

- አንድ ከመሆናችን በፊት መተው ተገቢ ነው።
- ቅድሚያውን ለትዳር አጋራችን መስጠት ይኖርብናል።
- የምንተወውን ማወቅ አለብን።
- እንቅፋቶቹን አውቆ ማለፍና መተው
- ያለመተው ከሚያስከትላቸው ችግሮች አንዱ የቤተሰቦች በትዳር ጣልቃ መግባትና ትዳሩን መበደል ነው።
- ለመተው ከሚረዱን ዘዴዎች መካከል አንዱ ከልጅነት ጀምሮ ዝግጅት ማድረግ ነው።

2. አንድ መሆን

- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው ባሎችም ሚስቶችም ድርሻቸውን ማወቅ። ኤፌ 5፡22-33።
- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው የሚከተሉትን አምስቱን ቃልኪዳኖች ዘወትር መጠበቅ
  - እግዚአብሔር አንድ ደደደረገውን ላለመለየት ቃል በመግባት። መቴ 19፡6
  - በመውደድና በማክበር
  - ደግና ርኅሩኅ የትዳር አጋር በመኖን
  - ዘወትር በመስጠት፣ ይቅር በማለት የጋብቻን ፍላጎት በማሟላት
  - የተቀደሰውን እግዚአብሔር የሚወደውን ሕይወት ለመያዝ ዘወትር ደካማነታችንን ወይም ደካማ ጎናችንን በመለወጥ ወይም በማሻሻል ነው።

ጋብቻ

የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች

1. መተው

- አንድ ከመሆናችን በፊት መተው ተገቢ ነው።
- ቅድሚያውን ለትዳር አጋራችን መስጠት ይኖርብናል።
- የምንተወውን ማወቅ አለብን።
- እንቅፋቶቹን አውቆ ማለፍና መተው
- ያለመተው ከሚያስከትላቸው ችግሮች አንዱ የቤተሰቦች በትዳር ጣልቃ መግባትና ትዳሩን መበደል ነው።
- ለመተው ከሚረዱን ዘዴዎች መካከል አንዱ ከልጅነት ጀምሮ ዝግጅት ማድረግ ነው።

2. አንድ መሆን

- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው ባሎችም ሚስቶችም ድርሻቸውን ማወቅ። ኤፌ 5፡22-33።
- አንድነቱ ጸንቶ የሚኖረው የሚከተሉትን አምስቱን ቃልኪዳኖች ዘወትር መጠበቅ
  - እግዚአብሔር አንድ ደደደረገውን ላለመለየት ቃል በመግባት። መቴ 19፡6
  - በመውደድና በማክበር
  - ደግና ርኅሩኅ ከራስ ይልቅ የሌላውን ጥቅም የሚያስቀድም/የምታ የትዳር አጋር በመሆን
  - ዘወትር በመስጠት፣ ይቅር በማለት የጋብቻን ፍላጎት በማሟላት
  - የተቀደሰውን እግዚአብሔር የሚወደውን ሕይወት ለመያዝ ዘወትር ደካማነታችንን ወይም ደካማ ጎናችንን በመለወጥ ወይም በማሻሻል ነው።

ጋብቻ

የጋብቻ ሦስቱ ገጽታዎች

3. መረዳዳት

- አንድነቱ የበለጠ ጥልቅ ስለሚሆን በሰማይ ወንድ ሴት የሚል ጸታ እንደሌለ ሁሉ በእርሱ በእግዚአብሔር በምድር የሚገኙ የእግዚአብሔር ይሆናሉ፡፡

- ደካማውን ሥጋ ለማሸነፍ በሁሉ መረዳዳት፡፡

- ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው መንገድ ሁለቱ አንድ ሆነው ተሳስረው መረዳዳት ናቸው፡፡

የዚህ ትምህርት ዓላማዎች

- የቅድመ ጋብቻን ትምህርትና ምክር አስፈላጊነት ማስገንዘብ

- የጋብቻን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት መረዳት

- ተጋቢዎች በዘወትር ህይወታቸው የሚገጥሟቸውን ችግሮችና ፈተናዎች ማስረዳት

- ለመተጫጨት፣ ለጋብቻ፣ ለፍቺ ወዘተ ቤተ ክርስቲያን የምትሰጣቸውን ትምህርቶች መረዳት ነው፡፡

... ክፍል ሁለት ይቀጥላል።

መስበሐት ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 2

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡- ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሚያዝያ ፮ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.

ጋብቻ

ባለፈው ሳምንት

1. በ1ኛ ዮሐ 1፡1 “ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን::” እንደ ተጠቀሰው ከጌታችን በማየት፣ በመስማትና በመማር ዘወትር ማፍቀር እንዳለብን
2. በኤፌ 5፡32 እንደ ተገለጸው ጋብቻ ታላቅ ምስጢር መሆኑን
3. ለቅዱስ ቁርባን ስለ ሚያስፈልገው ዝግጅት በ1ኛ ቆሮ 11 የተጻፈልንን ምሳሌ አድርገን ለጋብቻ ዝግጅት እንደያሚሻውና ከማግባትም በፊት ስለ ቅዱስ ጋብቻ በአግባብ መረዳታችንን ማረጋገጥ እንደሚኖርብን
4. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ጋብቻ መስጠትና መሥዋዕትነት እንደሆነ ከመግለጽ ጋር ጌታችን ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደዳት ባሎች ሚስቶቻቸውን መውደድ እንደሚገባቸው ሚስቶችም ቤተ ክርስቲያንን ለክርስቶስ እንደምትታዘዘው ለባሎች መታዘዝ እንዳለባቸው የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ተርጉሞ ማስረዳቱን
5. እስከ መተጫጨት ከጌታችን ጋር ጽኑ ወዳጅነት ማድረግ እንዳለብን፣ ከትዳር አጋር አንዱ ወደ ወዲያኛው ዓለም ቢጠራ እንኳ ከጌታችን ጋር ያለን ወዳጅነት ሳይበጠስ ተጽናንተን መቀጠል እንደሚያስችለን
6. ተጋቢዎች በጋብቻቸው ዕለት የመጀመሪያ ልጅ ጋብቻን እንደሚወልዱና ያ ልጅም በስሜት፣ በመንፈስ፣ በጥበብ፣ በአካል ማደግ እንደሚገባው፣ እንክብካቤና ማስታመምን እንደሚሻ
7. የእግዚአብሔር ቃል ጋብቻን ባለሥልጣን ሆኖ እንደሚመራው በዚህም መሠረት መተው፣ አንድ መሆንና መረዳዳት እንደሚኖር ተምረናል።

ጎሊና፣ የእምነት ሥርዓትና የተደበላለቀ ጋብቻ

- ጎሊና መንፈስቅዱስ አይደለም። *ዮሐ 17:3* የክርስቲያኖችን ዘላለማዊነት የሚያመለክት ሲሆን ከወላጆቻችን፣ ከአካባቢያችን የምንመለከተውን ተከትሎ ከ15 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ያድጋል ይበለጽጋል። ከ18 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ በጎ/ክፉውን ማስገባት/ማውጣት እንችላለን።
- የክርስቲያን ማንነት በተለያዩ መዋቅሮች ሲገለጽ
  - "የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።" *ቀዳ ተሰ 5:23።*
  1. የሰው አካል፡ የተለያዩ ሕዋሳት የሚገኙበት የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው።
  2. የሰው መንፈስ፡ መንፈስቅዱስ አይደለም።
     - መገኛው መንፈስቅዱስ ነው።
     - የሥነ ሕይወት ተመራማሪዎች ሊፈጥሩት የማይችሉት የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። አዳምን ሕይወት ያለው ያደረገው እግዚአብሔር ነው። *ዘፍጥ 2:7።*
  3. የሰው ነፍስ
     - ጠንቅቀን የማናውቀው ስሜታችንን ወይም ድርጊታችንን የሚቆጣጠር ለብዎ፣ ጎሊና፣ ፈቃድ፣ መሻት (ሐሳብ)፣ ስሜት
  4. መንፈስ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?" *ቀዳ ቆሮ 3:16።*

ጋብቻ


መንፈስ ቅዱስ
የሰው አካል
የሰው መንፈስ
ጠንቅቀን የማናውቀው ስሜታችንን ወይም
ድርጊታችንን የሚቆጣጠር ለብዎ
ጎሊና
ፈቃድ
አሳብ
ኃጢአት
ስሜት
መለኮታዊ ረድኤትና
ቅዱስ ሜሮን
ሰይጣንና ጽኑ ፈተናዎቹ
እንዲሁም
አንባቢና ሌሎችም

ጋብቻ

- ሥዕሉ እንደ ሽንኩርት ኮንሰንትሪክ ክብ ነው።
- የመጀመሪያው ሽፋን አካል ነው። ሁለተኛው ለአካል ሕይወትን የሚሰጠው መንፈስ ነው። ቀጥሎ የሚገኘው ነፍስ ነው።
- በጥልቁ የሚገኘው ስሜት ነው። እያንዳንዱ ሰው ሰባት መዋቅሮች አሉት።
- ስምንተኛው በተጠመቁ ኦርቶዶክሳውያን የሚኖር መንፈስቅዱስ ነው። መንፈስቅዱስ፦
  - የሰው ሁለንተናውን የሰይጣን ከሆነ ወጥመድ ይጠብቃል።
  - ተጠምቀን ቅዱስ ሜሮኑን ስንቀባ ይቀድሰናል።
  - ልጅነትን በጥምቀት መቀደስን በሜሮን ስናገኝ ወደ ዘላለማዊነት ያደርሰናል።
  - ክርስቲያኖች ያልሆኑ መንፈስቅዱስ ስለማይኖርባቸው ውስጣቸው ባዶ ወይም ቀፎ ነው።
- ሁሉንም መዋቅሮች ከመንፈስቅዱስ የሚለያቸው በሥዕሉ የሚታየው ጥቁሩ ክብ ነው። እርሱም ኃጢአት ሲሆን ብንበድልም በንስሐ የመመለስም ዕድል ተሰጥቶናል።
- መላ ነገራችን በመንፈስቅዱስ እርስ በርሱ ከተገናኘ የአምላካችን የመድኃኔዓለም መዓዛ ይኖረናል።
- አንድ ጠርሙስ ሽቱ ምን ያህል ውድ ነው? መላ ሰውነታችን እንደ ሽቱ ይሆናል።
- ኃጢአት በአንዱ ክፍል ውስጥ ከተገኘ መጥፎ ጠረን ይኖረናል።
- ከጌታችን ጋር የምንኖር ከሆንን እንደ ሽቱ የሆነ መዓዛ ይኖረናል በዚህም የተነሳ የእግዚአብሔር ሰው ሐሳባችንን፣ ድካማችንን፣ ጥረታችንን፣ መውጣት መውረዳችንን ... ያደንቅልናል። የክ

ኃብኽ

- በቤተ ክርስቲያን ምሰሶ የምናገኘውን የመስታወት/ክሪስታል እንውሰድ። ክሪስታሉ/መስታወቱ ጥርት ያለ ንጹሕ ነው። በጥምቀት የሚታደሰው ሰውነታችንም እንዲሁ ነው።

- ጤናማ ዓይን ያለው ሁሉ በእኛ ውስጥ የሚገኘውን መንፈስቅዱስ መመልከት ይችላል።
-
- በክሪስታሉ ላይ ጭቃ ከቀባን ብርሃኑን ማየት አንችልም። እኛ ስላልታየን ክሪስታል መሆኑ ቀረ ወይም ተለወጠ ማለት ግን አይደለም።
- ጭቃ የክሪስታሉን ውስጣዊ አካል ወይም የተሰራበትን ንጥረ ነገር ጠልቆ ሊገባ አይችልም። ጭቃውም ኃጢአት ነው።
- ኃጢአት አዲሱን ተፈጥሮአችንን ጠልቆ ገብቶ አይደመስሰውም። የሚያቆሽሰው የሚቻለውን የሚደርስበትን ነው።
- ክሪስታሉን ለማጽዳት እናጥበዋለን። እንዲሁ ወደ ንስሐ አባታችን በመሄድ በንሥሐ በመታጠብ ራሳችንን ከኃጢአት ንጹሕ ማድረግ ይኖርብናል።

- በንስሐ ከተመለስን የማይደመሰስ ኃጢአት የለም።
- በብርሃንና በጨለማ መካከል ምንም ጎብረት የለም፤ ይህን ግልጽ እውነታ በመረዳት ከጨለማ በመራቅ በብርሃን መመላለስና ብርሃንን መለበስ ያስፈልገናል።

ጋብቻ

- **እግዚአብሔር ለእኛ ማነው? በውስጣችን እንዴት እንስለዋለን? መድኃኒታችን፣ ሕይወታችን፣ አምላካችን፣ አባታችን ... ነው።**
- “ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል። ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን አይሰጣቸውን?” ... **ያለን ምን ያህል የፍቅር አምላክ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው።** ***ማቴ 7:7-9።***

- **ድምጹን ባልሰማን ጊዜ ለኢየሩሳሌም ለአይሁድም እንዳለቀሰ ያለቅሳል፣** “በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።” ***ዮሐ 10:27-31።***
- **በገዛ ፈቃዳችን እስካልተውነው ድረስ አይተወንም። በሮችዋ የተከፈቱ ቤተ ክርስቲያናችን ይህች ናት። የምታስተምረንም ይህንን ነው። በሮችዋን ከፍታ ወደ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሕይወት እንድንቀርብ ትጋብዘናለች።**
- **ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ምስጢረ ሥላሴ፣ ነገረ ድኅነት፣ ምሥጢረ ሥጋዌ፣ ዘላለማዊ ፍርድ፣ አማላጅነት፣ ቤተ ክርስቲያን... የምታስተምረውን አስቀድሞ መረዳት ለሁሉም ተገቢ ነው።**

ጋብቻ

ከጋብቻ አስቀድሞ፦

- ከዓለም ልጆች የተለየንና በሳል ጎሊና ያለን መሆናችንን በመመርመር ሰይጣን በሰለጠነ መንገድ የሚያስትበትን ጎዳና የተረዳን መሆን ይገባናል። ሰይጣንም የሚያስትባቸውን ዘዴዎች ቢያንስ በሚከተሉት መንገዶች ይገልጣቸዋል
    - የእግዚአብሔርን የቃሉን ሥልጣን በማቃለል
    - ራሳቸውን በሚቆጣጠሩ የተከበሩ ጎልማሶች እስከተፈጸመ ድረስ ወሲባዊ ግኑኝነት ነውርነት የለውም የሚሉ ወገኖችን በማደፋፈር
    - ልቅ የወሲብ ግኑኝነት ፊልሞች፦ የልጆችን ሕይወት መበዝበዝ፣ የሴቶችን ጉዳትና የቤተሰብን መበተን እንዲያስከትሉ በማድረግ፣
    - ሰዎችን ለማስደሰት የምንሄድባቸው ከሞራል ውጪ የሆኑ መንገዶች፣ በሃይማኖት አለመጽናት፣ በሥጋ የሚገኝ ደስታን እንደ መሠረታዊ ነገር መቁጠር፣ የእግዚአብሔርን እርዳታ እንዳንፈልግ የሚያደርጉ እንዲሁም ትሑት መሆንን የሚያጣጥሉ አካሄዶች በማለማመድ፣
    - መንፈሳዊ እውነታዎችን በአእምሮ ኃይል፣ በምትሐት፣ በልምድ ብቻ ለማግኘት እንድንጣጣር በማድረግ
    - ፓንቴይዝም "እንደ እግዚአብሔር ነህ" ዘፍጥ 3፡4፣ "ሁሉም እግዚአብሔር ነው እግዚአብሔርም ሁሉንም ነው" በሚሉ ዘመነኞች ከሃድያን እንድንማረክ በማድረግ፤
    - ተመልሶ በሌላ አካል ዳግመኛ ተወልዶ ወደዚህ ዓለም መምጣት አለ ብለን እንድናምን በማድረግ፣
    - "ላንተ መልካም የሆነ ለእኔ ላይሆን ይችላል፣ በዚህ ዓለም ፍጹም እውነት የለም መልካምና ክፉ ጓደኞች ናቸው" ብሎ በማሳመን።
    - "መዳን በልልምድ በሚደረግ ተመስጦ (Transcendental Meditation) ይገኛል፣ በልልምድ የሚደረግ ተመስጦም ዓይንን ይገልጣል" እያለ በማሳመን... ወዘተ

-

የተደበላለቀ ጋብቻ

- ጋብቻ መደበላለቁ የሚታወቀው፡-
  - በተለያየ ባህል፡ - ቋንቋ፡ አመጋገብ፡...፣
  - በተለያየ ሃይማኖት፣
  - በተለያዩ ቡድን ... የተነሳ ይሆናል፣
  - ያለመግባባት ምንጭ በመሆኑ፣
  - ውጤቱ መልካም ባለመሆኑ፣

የእምነት መዋቅሮቻችንና የተደበላለቀ ጋብቻን ራሱ ማጣጣም እንዴት ይቻላል?

- **የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን፡- የቀናች፣ ሐዋርያዊት፣ ትውፊታዊት፣ የራስዋ ቅዳሴ ያላት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊት፣ ገዳማዊት፣ በምስጢራት በአግባብ የምትጠቀም ክርስቲያን፣ ኢትዮጵያዊት፣ የተዋበች መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያን መሆንዋን ከጋብቻ አስቀድሞ በአግባብ በመረዳት**
- **ቤተ ክርስቲያናችን ለሁሉም ነገድ፣ ጎሳ፣ ዜጋ ቤተክርስቲያኒቱን ያውቃት ዘንድ በርዋ የተከፈተ ሁሉንም በደስታ ተቀብላ የምታስተናግድ የምታኖር መሆንዋን በማወቅ፤**
- **ሁሉም ቀርበው የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት፣ ትውፊት፣ ሃይማኖትና ሥርዓት አውቀው አምነው ሊከተሉዋት የሚችሉበት በር ክፍት እንደሆነ በማስተዋል፣**

- **ሁላችንም በቤተ ክርስቲያናችን ስለኖርን ቅዳሴውን፣ ሰዓታቱን፣ ማኅሌቱን ስንሰማ ያስደስተናል። የሚያስደስተን ቤተ ክርስቲያናችን ኢትዮጵያዊም ስላላበሰችው ጭምር ነው።**

ለተደበላለቀ ጋብቻ መፍትሔዎች

- ማንም ወደ አርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ሊገባ ቢሻ የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት፣ የመረጣቸውም የወዳጆቹ ምንነት፣ ሥርዓትዋ… ትምህርት በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ሊገለጥለትና ሊያምን ይገባል። ይህም ጋብቻ ስለሚመሠርት ብቻ መሆን የለበትም።

- የቤተ ክርስቲያናችን ድንበርዋ አድማስ ነው። በየትኛው ክፍለ አህጉር አለች። በአፍሪካ፣ እስያ፣ አውስትራሊያ፣ ሰሜን አሜሪካ፣ ደቡብ አሜሪካ ውስጥ ትገኛለች።

- በሌላ ቤት ቆይቶ ወደ ቤተክርስቲያናችን የሚመጡ የሚገጥማቸው ይኖራል። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴው ሦስት ሰዓት ይወስዳል፣ በካቶሊኮች አንድ ሰዓት ነው። ዲያቆን መባል ለሌሎች ቀላል ነው በቤተ ክርስቲያናችን ግን ሥርዓት ያለው ጎዳና አለ… ይህ በውጪ ሆነው የተለያየ ነገር ለለመዱ ቀላል ኤአደለም። ከመጡ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱን ተቀብለው መኖር ይጠበቃል።

- በዚህ ክፍለ ዘመን ያለ ፈተናን ተቋቁሞ ሌሎችን መታደግ ግን ከሁሉ ይጠበቃል።

ሁላችንንም ራሳችንንም ሆነ ሌላውን ለማነጽ የበቃን ያድርገን። አሜን!!!

... ክፍል ሦስት

“የሕይወት አጋርን መምረጥ”

ይቀጥላል።

መስከረም ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 3

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡ ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.

የሕይወት አጋር ምርጫ

- ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው በጌታችን በኀጢአት የጎሰቆለው የቀድሞ ሕይወታችን ታድሶ ተለውጧል። በበደልንም ጊዜ በንስሐ ታጥበን መልሰን እንነጻለን።
- ሰው ሁሉ በዚህ ዓለም የሚፈጽመው ተልዕኮና ይህንንም የሚያከናውንበት የሕይወት አቅጣጫ አለው።
- ***<u>ተልዕኮአችን ምንድር ነው?</u>*** ዘላለማዊ ሕይወት ነው። አቅማችን በፈቀደው መጠን ሁሉ ሰዎችን ወደ ዘላለማዊ ሕይወት ማቅረብ ወደ አባታችንም ወደ እግዚአብሔር እቅፍ ማስገባት ነው።
- ተልዕኮአችን የሚገጥሙንን ፈተናዎች ሁሉ ተቋቁመን በአምላካችን ጥበቃ ወደ ዘላለማዊት ሕይወት መድረስና ሌሎችንም ማድረስ ነው።
- ***<u>የሕይወት አቅጣጫችን ወይም ፍልስፍናችንም</u>*** እንደ ክርስቶስ ሆኖ መኖር ነው።
- ***<u>ሚናችን</u>*** ደግሞ እንደ ማንነታችን ይለያያል። ሚናችን አባት፣ እናት፣... መሆን ነው። በየሚናችንም የምናከናውነው የተለያየ ድርሻ አለን።
- እንደ አባት ሚስትን መውደድ፣ ልጆችን በፈሪሃ እግዚአብሔር ማሳደግ፣ ወዘተ ደግሞ ይኖራል። ይህም ግብ ነው። ***<u>ግብ</u>*** ከሕይወት አቅጣጫ (ፍልስፍናና) ከተልዕኮ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚጓዙ ናቸው።
- የአንዳንዱ ተልዕኮ ባለጠጋ መሆን፣ ተምሮ ብዙ ዲግሪዎችን መያዝ ይሆናል። ተልዕኮ ግን የሕይወት ፍልስፍናንና ግብን ይፈልጋል።

ጋብቻና ምንኩስና

- ሁለቱም የሕይወት መንገዶች የየራሳቸው ፈተና ያላቸው ሲሆኑ ጋብቻ ግን የተሻለ ምርጫ ነው።
- በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኒቂያ ጉባኤ በተደረገ ጊዜ ሕጋውያን (በትዳር የሚኖሩ) ቀሳውስትን ቀድሰው እንዳያቆርቡ ወደ ቤተመቅደስም እንዳይገቡ የሚያደርግ እንቅስቃሴ ነበር።
- ይሁን እንጂ በዚህ ጉባኤ ይህንኑ በጥልቀት በመመርመር ጋብቻ ታላቅ ምስጢር መሆኑንም በመረዳት በጋብቻ ነውር ሳይሆን ክብር እንደሆነ በማመን ለተፈጠሩት እንቅፋቶች መፍትሔ በማስቀመጥ <u>*ቅሰና*</u> ያገቡ ዲያቆናትም ሆኑ የማያገቡ መነኮሳትም የሚያገለግሉበት ሹመት እንደሆነ ወስነዋል።
- በካቶሊኮች ዘንድ ለካህናቶቻቸው በአጠቃላይ ማግባት አይፈቀድም።
- ለእናንተ የሚሻለው ጋብቻ ወይስ ምንኩስና?
- ለእኔ የቱ ይሻለኛል? ጋብቻ ወይስ ምንኩስና? በማለት የምንመርጥ ከሆንን በዚህ አካሄድ የምንገባው ለጋብቻ እንደሆነ እንረዳ። ምክንያቱም ለምንኩስና የሚገቡት ይኽን አሳብ ፈጽመው አያስቡም ትኩረትም አይሰጡትምና።
- መነኮሳት ጋብቻ ታላቅ ምስጢር ቢሆንም ለእኛ ግን አይደለም ብለው ምንኩስናን በመምረጥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ሙሽራ ይሆናሉ።
- መነኩሴ ለመሆን ከፈለግን ወደ ገዳም ከመሄዳችን አስቀድሞ በምንኩስና ሕይወት ለመኖር ከቤታችን ጀምሮ ዝግጅት እናድርግ።

ጋብቻና ምንኩስና

- ጋብቻም ምንኩስናም ሁለቱም የተመረጡ ሚናዎች ቢሆኑም ምንኩስና ግን ለተመረጡት እንጂ ለማንም እንደማይሆን መረዳት ያስፈልጋል። “በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው።” ***ማቴ 19:12።***
- ለሰው የተዘጋጀለት ምንድር ነው? ጋብቻ ነው።
- በምንኩስና ተለይተን ለመኖር ከመረጥን አስቀድሞ የንስሐ አባታችን በአግባብ ሊያውቁን ይገባል።
- የንስሐ አባታችን ፈቅደን ልባችን የተሰበረ መሆን አለመሆኑን መመርመርና ማወቅ ይኖርባቸዋል። ልብ ካልተሰበረ ይኽም በመንፈሳውያኑ አባቶች አስቀድሞ ካልተመረመረና ካልታወቀ ሕይወቱ ምንኩስና ሊሆን አይችልም።
- ጳጳስ እሆናለሁ ብሎ በማሰብ የተከፈለ ልብ ይዞ መነኩሴ አይኮንም። የቀሰቀሰን ምክንያት የተሳሳተ ነው።
- ለምንኩስና ሕይወት የሚያነሳሳን በላያችን በተዘጋው ባዕታችን ውስጥ ከሙሽራው ከጌታችን ከመድኃኔዓለም ጋር ለመሞትና ለመኖር መወሰን ነው።
- በምንኩስና ሕይወት ወደ ሙሽራው ወደ ጌታችን በሞት እስክንወሰድ ድረስ ገዳምን ትቶ መውጣት አይኖርም። ምንኩስና ማለት በጥቂቱ ይኸው ነው።

ለጋብቻ የሚያነሳሳን ምክንያት ምንድር ነው?

- ለጋብቻ የሚያነሳሱ ትክክለኛ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህም አንድ ሆኖ መረዳዳት፣ ዘር መተካትና ከፍትወት መጠበቅ የሚጠቀሱ ናቸው።

ለጋብቻ የሚያነሳሱ ትክክለኛ ምክንያቶች

- አንድ ሆኖ መረዳዳት። (1+1=1) "እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።" ***ዘፍጥ 1:28።***
- ዘር መተካት፡- ልጅ ቢኖረንም ባይኖረንም አንድነቱ ይቀጥላል። ልጅ ባይኖረን ወላጅ የሌላቸው ሁሉ ልጆቻችን ይሆናሉ። ልጆች መውለድ መንከባከብ ማታላችንንም መመርመር ይፈልጋል።
- ከፍትወት መጠበቅ (ንጽሕና)፡- "ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።" ቀዳ ቆሮ 7:9። "ዳሩ ግን ማግባት ወደሚገባው ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ስለ ድንግልናው ያፈረ ሰው ቢኖር፥ የወደደውን ያድርግ፤ ኃጢአት የለበትም፤ ይጋቡ።" ቀዳ ቆሮ 7:36።

ለጋብቻ የሚያነሳሱ የተሳሳቱ ምክንያቶች

- ፈቃደ ሥጋን መፈጸም

የሕይወት አጋራችንን እንዴት እንመርጣለን?

- መምረጥ 12 ሴቶችን ደርድሮ መምረጥ ነው???
- eHarmony የሚባል ዌብ ሳይት አለ። ማንነታችሁን ከፎቶግራፍ ጋር ልካችሁ እነርሱ ለናንተ የሚሆነውን መርጠው ይልካሉ። አንዳንዶች ቢንቁትም ማንነታቸውን ደብቀው ስምም ለውጠው የሚሞክሩ አሉ። www.heart-of-asia.com ለዚህ ጥሩ ተጠቃሽ ብዙዎች የሕይወት አጋር እናገናለን የሚሉበት የሞኝነት አዳራሽ ነው።
- ታዲያ የሕይወት አጋር አድርጌ የመረጥኩት የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን በምን አውቃለሁ?
- ያገባችሁ በምትማሩት ያለፉትን የሁለት ሳምንታት ትምህርት ጨምሮ ራሳችሁን መርምራችሁ አስተካክሉበት።

<u>የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አራት ቁልፍ መንገዶችና አሥር መመዘኛዎች አሉ።</u>

1. ***<u>የንስሐ አባት፦</u>*** ወደ ምናደርገው የሕይወት አጋር ምርጫ፣ ወደመተጫጨት ብሎም ወደጋብቻ የሚመሩን የንስሐ አባት መኖር። የንስሐ አባት መኖሩ የግድ አስፈላጊ ነው ይመራናልና። ከአባታችንም ጸሎታቸው፣ ትምህርታቸውንና የሚመሩንን አቅጣጫ ሁሉ የምንጠቀምበት መሆን ይገባናል።
    - ለንስሐ አባታችን ከነገርን ነገሩ እርግጠኛ መሆን አለመሆኑን በጥልቀት መርምረው ወደ አንድ አቅጣጫ ይመሩናል።

የሕይወት አጋራችንን እንዴት እንመርጣለን?

የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አራት ቁልፍ መንገዶችና አሥር መመዘኛዎች አሉ፡፡

2. ጸሎት፣ ጾምና ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፡-
    - ተረጋግተን ጸሎት በማድረግ፣ በመጾምና ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉንን በማንበብ ተረጋግተን ከተጓዝን ነገንም በእርጋታ መሻገር እንችላለን፡፡
3. የወላጆቻችን ምርቃት
    - ያለ ወላጆቻችን ምርቃት ትዳር ለመመሥረት መጣደፍ የለብንም፡፡
    - ከእግዚአብሔር የሆኑ ወላጆቻችን ነነልተቀበሉት ከሆነ በጋብቻው ችግር ይገጥመናል፡፡
    - የንስሐ አባቶቻችን ነነህን አስመልክቶ በእጅጉ ሲረዱን ይችላሉ፡፡
    - ስለዚህ የወላጆቻችንን ምርቃት እስክናገኝ ድረስ ያለንን ዕቅድ ሁሉ ማራዘም ይኖርብናል፡፡
    - መሆን የሚገባውን ይህን ጉዳይ ንቀን ብናልፈውና ነገ ወላጆቻችን በጋራ በአንድ ላይ በአንድ መርሐ ግብር ሲገኙ ምን እናደርጋለን? ለምሳሌ የአንዱ ወገን ወላጅ በሃይማኖቱ የጠነከረ ቢሆን ሌላኛው ደግሞ ምንም ባይረዳ ሲገናኙ የሚጨዋወቱት ስለምን ይሆን?...
4. መልካም አጋጣሚዎች
    - ዕቅዳችን ዕንቅፋት ሲሰለፍ ሌላ ዕንቅፋት፣ አንዱን የተዘጋ ደጅ ስናልፍ ሌላ የተዘጋ በር ደጋግሞ የሚገጥመን ከሆነ ውሳኔያችንን መመርመር ይገባናል፡፡
    - ነገር ሁሉ መልካም ከሆነም ከእግዚአብሔር እንደሆነ እንረዳ፡፡

የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

እነዚህ መመዘኛዎች ለውሳኔ ይረዳን ዘንድ የተሰጣቸው ፐርሰንት አለ። ፐርሰንቱም 100% መመሆናል።

- ከ75 — 100% ካገኘን ስጦታው ከእግዚአብሔር እንደሆነ እናውቅበታለን። ከ90% በላይ ግን የሚያገኝ አይኖርም

1. መንፈሳዊ ሕይወት (አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ሕይወት)
   - በየዕለቱ ቤተ ክርስቲያን መምጣታችንን፣ አገልጋዮች መሆናችንን፣ ዘወትር መጸለያችንን፣ በየሳምንቱ መቁረባችንን፣ ... ማለት ኤአደለም። ከዚያ ያለፈ ነው።
   - አመለካከታችን፣ አስተሳሰባችን፣ ከአንደበታችን የሚወጡ ቃላቶች፣ ጠባያችን፣ ስሜታችን ... ወዘተ አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ እርሱን የሚያስመስለን ነው?
   - በየዕለቱ ቤተ ክርስቲያን መምጣታችንን፣ አገልጋዮች መሆናችንን፣ ዘወትር መጸለያችንን፣ በየሳምንቱ መቁረባችንን፣ ... ብቻ በቂ ኤአደለም።
   - አመለካከታችን፣ አስተሳሰባችን፣ ከአንደበታችን የሚወጡ ቃላቶች፣ ጠባያችን፣ ስሜታችን ... ወዘተ የተቀደሰ ካልሆነ አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ያደረግን እርሱንም የምንመስል አይደለንም።
   - እውነተና አገልጋይ በቤት ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስት ሳይሆን ትክክለኛና ግልጥ በሆነው በራሱ ማንነት ውስጥ የሚገኝ ነው።
   - በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ መጠጥ የሚያቀርቡ፣ ዕፅ የሚመመዘዋውሩ፣... የሚጠነቁሉ የሚያስጠነቁሉ ይኖራሉና መጠንቀቅ ይኖርብናል።

የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

- ልቅ የሆኑ የወሲብ ፊልሞችን የተለማመዱ ብዙዎች ይኖራሉና መጠንቀቅ ይገባል።
- አምላካችን ክርስቶስን ማዕከል ማድረግ እርሱንም መምሰል በነፍሳችን በመንፈሳችንና በሥጋችን የርሱን ምሳሌነት መከተል ነው።
- ነገሮችን ሁሉ በርጋታ ተቀምጠን እንመርምር።
- ይሕ መመዘኛ ብቻውን 50% ይይዛል።
- ከ2 — 10 ያሉት መመዘኛዎች ቅደም ተከተል የላቸውም። እንደ ፍላጎታችሁ ቅደም ተከተል ስጡት። በአጠቃላይም 45% መመህሉን ድርሻ ይይዛሉ።

2. ቤተሰብ
   - የርሷና የኔ ቤተሰብ ተቀላቅሏል? አንዱ ሌላውን መገንዘብ ይችላል?
   - በአንዳንድ ማኅበራዊ አጋጣሚዎች በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ተነጋግረው መግባባት ይችላሉ? በአስተሳሰብም ሆነ በአመለካከት መቀዳደም የለም? ስለ ቤ/ክ፣ ስለ ቅዱሳን የሚነጋገሩት ያግባባቸዋል?
   - ከቀለበት በፊት የሌላውን ወላጅ ለመጎብኘት እንሄዳለን? አዎ ሁለቱ ሦስቱ ቢበበንስ መሄድ ይጠበቅብናል።
   - በአንዳንድ ጉዳዮች ባለመግባባት አንዱ ዝም ብሎ ተናጋሪ አንዱ አዳማጭ እየሆነ መመጣጠን የሚጠፋባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ።

የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

3. ከሰው የመግባባት ችሎታ
   - ማዳመጥ፣ መረዳት፣ ራስን መግለጥ፣ ...
   - አብረን ስንቀመጥ መግባባት እንችላለን?
   - አንተ/እርስዋ ንግግራችሁ ያበሳጫችኋል?
   - እርስዋ ስለ ኢኮኖሚክስ የመመረቂያ ጥናትዋ ወይም ምርምርዋ ልታስረዳ ልትናገር ትችላለች። ነገር ግን ይኽ ያግባባናል? መደማመጥ እንችላለን?
   - በዚህ ሂደት አንዱ ሌላውን የመመዘን ዕድል ያለው ሲሆን የመግባባት ችሎታችንንም ደረጃ ይገልጣል።
4. ስሜትን መግለጽ
   - ስሜትን መቆጣጠር መቻል።
   - የተዘበራረቀ ስሜትን፣ ንዴትን፣ ብስጭትን፣ ሁከትን፣ ርኅራኄን፣ መነካታችንን የምንገልጽባቸው መንገዶች ብስለት
5. በማኅበራዊ ሕይወት ያለን ብቃት
   - ከሰው ጋር መቀራረብ፣ ጓደኞቻችን ጋር ያለን መቀራረብና መራራቅ፣ ...
   - ጋብቻን ለመመሥረት ካሰብን ራሳችንን መቆጣጠር ባልቻልንባቸው ምክንያቶች፣ አደንዛዥ ዕፅ በመጠቀምና ባለመጠቀም፣ ቁማርን፣ ያልተገደበ ወጪያችንን፣ ወዘተ በተመለከተ ያለንን ብቃት እንገምግም።

የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

6. ኃላፊነት የሚሰማን መሆንና ቅንነት
   - ልጆችን፣ ቃላችንን፣ ጠባያችንን በተመለከተ እምነት የሚጣልብን ነን?
   - የንስሐ አባታችን እርሱ እምነት የሚጣልበትና ቅን ሰው ወይም እርሷ እምነት የሚጣልባት ቅን ሰው ስለመሆኗ ሙሉ በሙሉ ምስክርነት ልሰጥ እችላለሁ ይሉልናል?
   - ውስጣዊ ብስለታችን ምን ያህል ነው?
7. የሥራችንና የምናገኘው ገቢ ሁኔታ የተረጋጋ መሆን
   - ፍቅር ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለም ለመኖር የምንሠራው ሥራ፣ ሠርተን የምናገኘው ገቢ ያስፈልገናል።
   - ወደ ጋብቻ ሕይወት ለመግባት የራሳችን ሞያ ወይም ዕውቀት ያለን መሆን አስፈላጊ ነው።
8. ተክለ ቁመናና መልክ
   - ምን ያህል ቆንጆ ወይም ውብ፣ ረጅም ወይም አጭር፣ ጥቁር ጠይም ወይም ቀይ፣ ወፍራም ወይም ቀጭን መሆንን መምረጥ

ማስጠንቀቂያ

- በዚህ መመዘኛ ብቻ ከ90-100% ሰጥታችሁ ያገኙ ካሉ ባታገቡ የተሻለ ነው። ምክንያቱም በፍትወት ብቻ መሳባችንን የሚያሳይ ስለሆነ ነው። ዳሌ፣ ቀለም፣ ወገብ የምንመርጥ ከሆንን እንጠንቀቅ።

የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

- ይህን የፈለግነውን ዓይነት ውበት የተለያዩ ኮስሞቲኮችን ወይም ፕላስቲክ ሰርጀሪ በማድረግም ቢሆን ማምጣት ይቻላል፡፡... ቀድመን ያላወቅነውን ሰው ሠራሽ ጥርስ አውልቆ መተኛትን ከጋብቻ በኋላ ስናውቅ መደንገጥ እንዳይኖር ይኽን መመዘኛ ከሌላው የበለጠ ላለማድረግ እንጠንቀቅ፡፡
- ብዙ ሺ ብር በማውጣት ለመንፈሳዊ ሕይወት ግን ፕላስቲክ ሠርጀሪ ማድረግ አይቻልም፡፡
- ስለዚህ ዓይናችንን ከድነን ለሕይወት አጋርነት በመረጥነው/በመረጥናት ውስጥ ምን እንዳለ በጥልቀት እንመልከት፡፡
- በውጪው ውበት ላይ እጅግ አትኩሮት የምናደርግ ከሆንን አእምሮአችን መቆሸሹን እንወቅ፡፡
- የአፍንጫዋ ቀዳዳ አንዱ ከአንዱ ይበልጣል አንዱ ሰፋ ይላል ብለው ሌላውን ጥሩ ገጽታ ንቀው በምርጫቸው የሚሳሳቱ አሉ፡፡
- ዛሬ አንዳንዶች የተዘፈቁበት ልቅ የሆነ የወሲብ ፊልም የትዳር ገዳይ ነው፡፡ ይህም የቅድስና መታጣት ምልክት ነው፡፡

9. ጤንነት

- ስኳር፣ ጉበት፣ ካንሰር፣... ወዘተ ካለ ሳይደበቅ መቀለጥ መቻል አለበት፡፡
- አንዳንድ ጊዜ ሳቀቀነገር ቀርቶ የተደበቀ በሽታ ትዳሩን ይጎዳልና አስቀድሞ ታውቆ ተነጋግሮ መፍትሔ እንዲደረግለት ይገባል፡፡

የሕይወት አጋራችንን የምንመርጥባቸው አሥሩ መመዘኛዎች?

10. አእምሮአዊ ጤንነት

- የአእምሮ ጭንቀት፣ እብደት... ወዘተ ያለ መሆን አለመሆኑን ቃል ኪዳን ከመግባታችን፣ ፊርማችንን ከማኖራችንና፣ ከመፈራረማችን በፊት ማረጋገጥ - ከተጋቡ በኋላ መፋታት የለምና።

- ሌሎች ያልተጠቀሱ መታየት ያለባቸው ጉዳዮች ሳይጋነኑ ሊታከሉ ይችላሉ።

- ከ2 — 10 ያሉትን ለእያንዳንዳቸው 5% እየሰጠን ብንደምራቸው 45% ይሆናሉ።

- እኛ በራሳችን ገምግመን የተዋጣልን ስለማንሆን የተረፈውን 5% ለራሳችን እንስጥ።

- ከዚህ በላይ ያሉትን መመዘኛዎቻችንን ይዘን በሕይወታችን ሁሉን ወደ ሚመሩ ሁሉን ወደሚወስኑ የንስሐ አባቶቻችን ይዘን በመሄድ በመጨረሻ ውሳኔያችን የተጣራ ውጤት ያለን እንሁን።

- እግዚአብሔር የሕይወት አጋርን በወላጆቻችን፣ በጓደኞቻችን ... አቅራቢነት ወይም አማካይነት ሊሰጠን ይችላልና የምንንቀው የእግዚአብሔር ሥራ አይኑር።

- ከዚህ ባለፈ መመዘኛችንንም ሆነ ተመዛጮችን አናብዛ... እንዳንችገር።

... ክፍል አራት ይቀጥላል።

መስብሐት ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 4

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡ **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሚያዝያ ፳ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.

የቀድሞ የሕይወት ታሪካችንና ጋብቻ

- የዛሬው ትምህርት የቀደመ መጥፎ ታሪክና ስለጋብቻ ሲሉ መጥፎውንም ገጽታ የማጽዳትን አስፈላፊነት የሚያመላክት ነው።
- ያን መጥፎ አጋጣሚ በጊዜ፣ በቦታ ወስነን ማስታወስ እንችላለን? ያ ታሪክ ሲፈጸም እግዚአብሔር በሕይወታችን በየት ነበር? እርሱ ቢኖር መጥፎው ታሪክ እንዴት ሊለወጥ ይችል ነበር?
- ያ መጥፎ ታሪክ ሲከሰት የነበሩትን ወይም ለጉዳቱ መንሥኤ የሆኑትን እናስታውሳቸዋለን? ይቅርስ እንላቸዋለን? ይቅር የማይሉ ሰዎች እንቅልፍ የላቸውም።
- ልጃችንን በመኪና የገደለውን ሰው በቀላሉ የማንረሳው ቢሆንም ይቅር ማለት ግን ይገባናል።
- የቀድሞ ሕይወታችን በዛሬው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህንም አስመልክቶ አሥር ነጥቦችን እንመለከታለን።

1. ባለፈ ሕይወታችን የደረሰብን ጉዳት ወይም አደጋ ምን ነበር? ማቆምስ እችል ነበር ወይ?
2. ባለፈ ሕይወታችን ያሳለፍነው ንዴት ምን ነበር?
3. የቀደሙ ቤተ ሰቦቻችን እነማን ነበሩ?
4. ትምህርት የተማርንበት ወይም ከፍተኛ ትምህርት የተከታተልንበት ተቋም የቱ ነበር?
5. በጸታዊ ጉዳይ ያለፈ ታሪካችን ምን ይመስል ነበር?
6. የሥራ ዘርፋችን ወይም መደባችንና ሥራውን ለመሥራት የሚያስችለን መያዊ ብቃት ምን ነበር?
7. ከዚህ በፊት ከጓደኞቻችን ጋር የነበረው ግኑኝነት ምን ይመስል ነበር?
8. የገንዘብ አቅማችንና የገቢ ምንጫችን ምን ይመስል ነበር?
9. አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነታችን ምን ይመስል ነበር?
10. መንፈሳዊ ሕይወታችንስ ምን ይመስል ነበር?

1. ባለፈ ሕይወታችን የደረሰብን ጉዳት ወይም አደጋ ምን ነበር?

- የቃልም ሆነ አካላዊ ጉዳት ደርሶብን ተጎድተን እናውቃለን?
- በሌሎች ላይ የቃልም ሆነ የአካል ጉዳት አድርሰን እናውቃለን?
- ከዚህ በፊት የጎዱንን ሰዎች ፊት ለፊት ልንገናኛቸው የምንችልበት ጥንካሬ አለን?
- የጉዳቱ ጠባሳ ቢኖርም በመንገድ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ ወዘተ ልንገናኝ እንችላለን።
- እስካሁን ድረስ ከጉዳቱ ጋር በተያያዘ የምናስታውሳቸው ስሞች አሉን?
- ስማችንን ጠርተው የሚሰድቡን፣ ጫማ ወዘተ የሚወረውሩብን ገጥመውን ያውቃሉ?
- አንዳንዶች የመደፈር ወይም ክርስቲያናዊ ባልሆነ መንገድ ለዝሙት የመጋበዝ ትንኮሳ የገጠማቸው ይሆናሉ።
- ይህም ሁለት ሦስት ጊዜ በተደጋጋሚ ገጥሞን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የገጠመን የት፣ መቼ፣ እንዴት ነው? ያን ጉዳት ማከም ችለናል? እንዴት ታከምነው?
- የሴቶች ግርዛት ራሱ በደል ወይም ጉዳት ማድረስ አድርጎ ይቆጠራል። በመጽሐፍ ቅዱስም አልተፈቀደም። በግርዛቱ ጊዜ የተፈጠረው የደም መፍሰስም ብዙዎችን ጎድቷል።
- ፍቅር ፈልገን ስንቀርብ ለበጎ የፍቅር ጥያቄያችን መልካም ምላሽ የሚሰጠን አጥተናል? እርዳታ፣ ርኅራኄን ፈልገን የሚመልስልን አጥተን እናውቃለን? እስካሁን ካስታወስነው ጎጂ ነው።
- ጉዳቶቹንስ ስናስባቸው ሕመሙ አሁንም ድረስ ይሰማናል?
- ዛሬም ቢሆን የተለያዩ ጥቃቶች በየቤቱ የሚከሰቱ አሳዛኝ ታሪኮች ናቸው።

2. ባለፈ ሕይወታችን ያሳለፍነው ንዴት ምን ነበር?

- በራሳችን፣ በሌሎች እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ የነበረን ንዴት ምንድር ነበር?
- <u>በራሳችን</u>፡- የኛ ኃላፊነት ባልነበረበት ጉዳዮች ንዴታችን ምንድር ነበር? አንድን ነገር ስናስታውሰን ያናድደናል? ራሳችን የሠራናቸውን ስህተቶች ስናስታውሳቸው በራሳችን ተናደን እናውቃለን?
- <u>በሌሎች</u>፡- መግለጽ ወይም ማስረዳት የምንችልበት አጋጣሚ በማጣት ወይም ባለመቻላችን፣ በተከሰተውም ሁኔታ በጣም በመናደዳችን፣ ወዘተ የተናደድንባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ? ይህ ራስን ወደማጥፋት ሊያመራ ይችላል።
- እነዚህን ሰዎች ዛሬም ድረስ በሕይወት ካሉ ጤናማ በሆነ መንገድ ልንግባባቸው እንችላለን?፣ ለነዚህ ጉዳት ላደረሱብን ሰዎች ደብዳቤ ጽፈን ምን ያህል እንደጎዱን ገልጸንላቸው እናውቃለን?
- <u>በእግዚአብሔር</u>፡- የሕይወት ጓደኛዬ እንዲሞት/እንድትሞት ለምን ፈቀደ? ራሱን/ራሷን አጥፍታ ሊሆን ይችላል? ታዲያ እጊዚአብሔር ይህን ለምን ዝም አለ? ታዲያ ርኅራኄው የበዛ እግዚአብሔር ይህ ነው?
- ካንሰር እንዲኖርብኝ ስለምን ፈቀደ? አደረገ?
- ስንት ዘመን ሙሉ በጸሎት እየጠየቅሁህ እንደዚህ ዓይነት መከራ የማይበትን/የማይባትን ሰው/ሴት እንዳገባ ስለምን አደረግኸኝ?
- ሚስትህ ስለሞተች በእግዚአብሔር ተናደሃል?
- ባልሽ ስለሞተ በእግዚአብሔር ተናደሻል?
- ልጆች ስለሞቱባችሁ ወይም ስለታመሙባችሁ በእግዚአብሔር ተናዳችኋል? ችግሩ አሁን ተፈቷል?

3. የቀደሙ ቤተ ሰቦቻችን እነማን ነበሩ?

- ወላጆቻችን የሚከባበሩ ሆነን የመመልከት ዕድል ነበረን?
- ወላጆች፡- በአባትና እናታችን መካከል የነበረው የትዳር ሕይወት ምን ይመስል ነበር?
- አባት ሁልጊዜ አዛዥነት የሚያዘወትሩ ነበሩ? ጠጪስ ነበሩ?
- በወላጆቻችን መካከል የነበረው ግኑኝነት ልናስታውሰው የማንፈልገው መጥፎ ነበር?
- ከቤተሰቦቻችን የተነሳ ደኅንነት ወይም ዋስትና እንክብካቤ የማጣት ወይም ስሜት ይሰማን ነበር?
- ወላጆቻችን መልካም አርአያዎቻችን ነበሩ? በነገሮች የሚያበረታቱን ነበሩ ወይስ ዘወትር የሚወቅሱንና የሚጎዱን?
- ወላጆቻችን በእኛ ላይ ትዕግሥተኞችና የሚችሉን ነበሩ?
- ወላጆቻችን በቂ እንክብካቤ፣ ፍቅርና ርኅራኄ ያሳዩን ነበር?
- እናታችን አቅፋን የሳመችበት፣ አባታችን በጉልበቱ ላይ ያስቀመጠበት... ጊዜ ይታወሰናል?
- ጓደኞቻችን ወደ ቤታችን እንዲመጡ ይፈቅዱ ነበር፣ ሲመጡስ ያከብሯቸው ነበር?
- በቤተ ሰቦቻችን ወይም ጓደኞቻችን ፊት በሚጎዳን መልኩ ይቀጡን ነበር?
- ከወላጆቻችን ጋር ያለን ግኑኝነት መነጋገር ላይ የተመሠረተ ነው? ወይስ በመስማት ላይ ብቻ?
- ባንወዳቸውም አሁን ያለን ማንነት እንደ አባታችን ወይም እናታችን ያለ ነው? ለምን፣ ጠባያቸውን የማንወደው ከሆንን ለምን መልሰን እንደነርሱ እንሆናለን?
- ስለዚህ ይህን የትናንት መጥፎ ገጽታ እንዴት እንደምናሻሽለው እገዛን እንፈልግ።
- ከቤተሰቦቻችን ጋር ያለን ግኑኝነት እውነተኛ፣ ሁሉንም መውደድ ያለበት ነው ወይስ ባለጠጎቹን ለይተን.... የምንወድበት ሌላውን የምንጠላበት ነው?

4. ትምህርት የተማርንበት ወይም ከፍተኛ ትምህርት የተከታተልንበት ተቋም የቱ ነበር?

- ትምህርት ቤቱ ምን ተብሎ ይጠራ ነበር? ማጥናት የምንፈልገው የትኛው ዩኒቨርስቲ ገብተን ነው?
- በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለን ሲደበድቡን የነበሩ መምህራንን እስካሁን እናስታውሳቸዋለን?
- በትምህርት ቤት እያለን ጥቃት ያደረሱብን መምህራን ቢኖሩስ ይታወሱናል?
- መጥፎ የትምህርት ቤታችን ስሞች አሁንም አይለየንም፣ ውጤታችን፣ መጥፎ ውጤት ስናገኝ ይደርስብን የነበረው መገለል፣ ወዘተ አሁንም አብሮን እየጎዳን አለ?

5. በጾታዊ ጉዳይ ያለፈ ታሪካችን ምን ይመስል ነበር?

- ከጾታ አጋሮቻችን ጋር ጤናማ ግኑኝነት እንዲኖረን ሆነን አድገናል?
- ከማግባታችን በፊት በሰንበት ት/ቤት እያለን ከተቃሪኒ ጾታ ጋር ጤናማ ያልሆነ ግኑኝነት ነበረን?
- በጾታ የሚመስሉን መጥፎ የመረጃ ምንጮችን ሰጥተውን እምቢ ሳንል ቀርተን ተቀብለናል?
- ልቅ የወሲብ ፊልሞችን በመመልከት የተፈጠረብን ተጽእኖ አለ? ሳናደርግስ ስላለፈን እንቆጫለን?
- ራሳችንን በተመለከተ በጣም ቶሎ ስሜት ውስጥ የምንገባ ወይም የምንዘፈቅ ነበርን?

6. የሥራ ዘርፋችን ወይም መደባችንና ሥራውን ለመሥራት የሚያስችለን መያዊ ብቃት ምን ነበር?

- በምንሠራው ሥራ ወይም በአከናወንነው ነገር ውጤታማና የተሳካልን ነበርን?
- በዚህም የተነሳ ስለወደፊቱ ያለን ተስፋ የለመለመ ነው?
- በተሰማራንበት የሥራ መስክና ባለን ሙያ መመጣጠንና መረጋጋት አለን?
- ሥራችንን መቀየር እንፈልጋለን ወይስ ተመችቶናል? በሄድንበት ለቃል ጥያቄ ወይም ለኢንተርቪው ማለፍ አቅቶን የምንቸገር ነበርን ወይስ ሁልጊዜ የምንመረጥ?
- በሥራችን ጉዳይ አለቆቻችን ያለ አግባብ ይወስኑብናል ወይስ ስለ ሥራችንና ስለ ብቃታችን አድንቀው ያመሰግኑናል?

7. ከዚህ በፊት ከጓደኞቻችን ጋር የነበረው ግኑኝነት ምን ይመስል ነበር?

- ጓደኞች ነበሩን፣ ምን ዓይነት፣ መትፎ ሱስ አለን...? ለእድገታችን ምክንያት ናቸው ወይም ለመበላሸታችን?
- ከቤት ውጪ ስንሆን ለመዝናናት ስንወጣ የምናደርገው ምንድር ነው?
- በሱሰኝነት የተያዝንበት መጥፎ ሁኔታ አለ?
- መልካም ባልሆኑ የስሜት ፍትር ድርጊቶች የምንታወስ ነን? ቃል ኪዳን አፍርሰን እናውቃለን፣ ከዚህም ከዚያችም ጋር ግልጽ በሆነ መንገድ በመውደቅ መታወቂያ ምልክት የተሰጠን ነን?

8. የገንዘብ አቅማችንና የገቢ ምንጫችን ምን ይመስል ነበር?

- እስካሁን ድረስ የምንከፍለው ብድር ወይም ዕዳ አለብን?
- ጥቂትም ቢሆን የምንቆጥብበት የቁጠባ የሂሳብ ደብተር አለን?
- ገንዘባችንን ወይም ገቢያችንን ያለአግባብ እንጠቀማለን? ወሩ ሳይደርስ ደመወዛችንን በመብላትና በመጠጣት የምንጨርስ ነን?

9. አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነታችን ምን ይመስል ነበር?

- መላ አካላችንና አእምሮአችን ጤናማና በአግባብ ማከናወን የሚችል ነው?
- መጠጥም ሆነ ሌላ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ ምክንያት ትክክለኛ እንቅስቃሴውያችንን የገደበው አይደለምን? ከጋብቻ በፊት ብንመረመረው መልካም ነው ብለን እናምናለን?

10. መንፈሳዊ ሕይወታችንስ ምን ይመስል ነበር?

- በእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ያደግን ነን? ሃይማኖታችንን ትተን የሄድንበት ወይም ሃይማኖታችንን የለወጥንበት ጊዜ ነበር?
- ለጸሎት፣ ቅዳሴ ለማስቀደስ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ፣ ለመማር፣ ወዘተ የተመደበ የታወቀ መርሐ ግብር አለን?
- የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ይሰማናል? የንስሐ አባት አለን? የንስሐ አባታችን የሚሰጡንን ምክር እንከታተላለን? ማንኛውንም ጉዳይ በግልጽ ለነፍስ አባታችን ገልጸን እንነጋገራለን?

- እነዚህ ሁሉ ያልታረሙ የቀድሞ ታሪኮችን ጉዳዮች በአእምሮአችን እያሉ ወደ ትዳር ለመግባት አንድፈር።
- ከገባንም ያልታረመውን የሕይወታችንን ችግር ከንስሐ አባታችን ጋር ተነጋግረን እናስተካክለው።
- በሁሉ የእግዚአብሔር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን።

ምንባብ

- “ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፦ አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ። 10 31 ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም ገለል ብሎ አለፈ። 10 32 እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ስፍራ መጣና አይቶት ገለል ብሎ አለፈ። 10 33 አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥ 10 34 ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቍስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፥ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደርያ ወሰደው ጠበቀውም። 10 35 በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና። ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው። 10 36 እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል? 10 37 እርሱም፦ ምሕረት ያደረገለት አለ። ኢየሱስም፦ ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው። ***ሉቃ 10:32-37።***
- “ተንበርክኮም። ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።” ***የሐ. ሥራ 7:60።***
- “ኢየሱስም፦ አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።” ***ሉቃ 23:34።***

E-mail:
kesisolomon3@gmail.com

Web Site:
www.zeorthodox.org

... ክፍል አምስት ይቀጥላል።

መስብሐት ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 5

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡ **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ግንቦት ፲፩ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

- የዛሬው ትምህርታችን ማዕከል ጥንታዊና ጥንታዊውን ያልሆኑ የክርስቲያን ቤተሰቦች ሕይወት መመልከት ነው። ትዳራችን ጥንታዊ ገጽታ ያለው እንዲሆን እንሻለን ወይስ ጥንታዊ ያልሆነ ገጽታ ያለው?
- በዚሁ ትምህርት የወንድና የሴትን ድርሻ፣ በትዳር ሕይወት ስላለ መሪነት/መጋቢነት፣ ወንድነት ወይም ሴትነት ምን እንደሆነና በምን እንደሚገለጽ፣ በትዳር ሕይወት ወሳኙ ማን እንደሆነ... በእግዚአብሔር ፈቃድ እንማራለን።

<u>የወንድና የሴት ድርሻ</u>

I. ***<u>ጥንታዊ ቤተ ሰብ</u>***

1. ወንድ
   - ራስ (መሪ) ነው። በእርግጥ እውነተኛው የሁሉ መሪ ክርስቶስ ነው።
   - ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ሰጪ መጋቢ ነው። ፍቅር፣ የልጆች አስተዳደግ...
   - ባል ነው።
   - አባት ነው።
2. ሴት
   - ሚስት ናት።
   - የቤት እመቤት ናት። የቤቱ ሥራ የሚበዛው የርስዋ ነው... ወንድ ማዕድ ቤት ቢገባ እንደ ነውር ይታሰባል...
   - እናት ናት።

II. የ"ኢንዱስትሪ አብዮት" ሠራተኞች እናቶችን ፈጥሯል። ይህም የቤተ ሰብንና የትዳር ሕይወትን መልክ ቀይሮ ጥንታዊ ገጽታው ሌላ መልክ እንዲይዝ አድርጎታል።

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

III. ***ዘመናዊው ወይም ጥንታዊ ያልሆነው ቤተ ሰብ***

1. ወንድ
    - ራስ (መሪ) ነው። በእርግጥ እውነተኛው የሁሉ መሪ ክርስቶስ ነው።
    - ሰጪ ነው።
    - ባል ነው።
    - አባት ነው።
    - የቤት ሥራ ይሠራል። ጥገና፣ አናጢነት፣ ልብስን መተኮስ ... ልጆችን ይንከባከባል፣ ልብስ ያጥባል።
2. ሴት
    - ራዳት መሪ ናት። ልክ እንደ ረዳት አውሮፕላን አብራሪ...
    - ሰጪና ሠራተኛ ናት።
    - ሚስት ናት
    - የቤት እመቤት ናት።
    - እናት ናት።

- ለእኛ ትዳር የሚሠራው የቱ ነው? ጥንታዊው ነው ወይስ ጥንታዊ ያልሆነው? ሳያውቁ ሁለቱን ማቀላቀል ወይም ማደበላለቅ አደጋ ያስከትላል።

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

IV. የጋብቻ ዓይነቶች

1. ቋሚ (መንፈሳዊ/እውነተኛ)፦ ትክክለኛው የትዳር ዓላማና ግብ ላይ አትኩሮት ያደርጋል። ለምሳሌ በትዳሩ ቀዳሚው እግዚአብሔር ነው፣ የሚከተሉትም ሚስት/ባል፣ ልጆች፣ ወላጆች... ወዳጆች፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት፣ ወዳጆቻችን... እዚህ ላይ የ"ሕንድ" ፊልም ላይ የምናያቸው ዓይነት መንገዶች አይሠሩም...
2. ቁሳዊ፦ ገቢን፣ ወጪን፣ ወዘተን ይመለከታሉ... ውጤቱም መድረቅ መበስበስ መቀጨጭ ነው።

- ስለዚህ የሚቀድመውን ቋሚውን ማስቀደምና ከቁሳዊውም የሚካተቱትን ማወቅና መለየት ይኖርብናል።

V. መሪነትና ራስን መስጠት

I. ልብና አንጎል

- "ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ልታውቁ እወዳለሁ። ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ ራሱን መከናነብ አይገባውም፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት። ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም ያለ ሴት አይሆንም። ሴት ከወንድ እንደ ሆነች እንዲሁ ወንድ ደግሞ በሴት ነውና፤ ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው።" ***ቀዳ ቆሮ 11:3፣7፣11፣12።***
- ሴት የተገኘችው ከወንድ ከአዳም ነው፣ አዳም ሰውም የተገኘው ከእግዚአብሔር ነው። ይህም ባርነትን አያመለክትም። ባል ከእርሱ ለተገኘችው ለሚስቱና ለልጆቹ ኃላፊነት አለበት። የከበደውንና ከአቅሙ በላይ የሆነውን ወዳስገኘው ወደ እግዚአብሔር ያቀርብና መፍትሔ ያገኝበታል።
- "ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ። ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ። ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤...

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

… እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል።" ***ኤፌ 5:21-29።***

- ከላይ በተጠቀሰው የመጽሐፍ ክፍል የሴቶች ድርሻ ሦስት የወንዶቹ ደግሞ በርከት ብሎ ስድስት ነው።
- ራስነት አንዱን ትልቅ ሌላውን ታናሽ አያደርግም። በምስጢረ ተክሊል ሲጋጠሙ እያንዳንዳቸው ሙሉ ይሆናሉ። እርሱ ያለርሷ እርሷም ያለርሱ ጎዶሎ ናቸው።
- ባልና ሚስት በእግዚአብሔርም በልጆቻቸውም ፊት በትዳር እኩል ቢሆኑም በተሰጣቸው ድርሻ ግን ይለያያሉ።
- "ሚስቶች ሆይ፥ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ። ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው።" ***ቆላ 3:18-19።***
- "እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሃት ያለውን ንጹሑን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው። ለእናንተም ጠጕርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ።… እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።" ***ቀዳ ጴጥ 3:1-4 እና 3:7።***
- ቅዱስ ጴጥሮስ ባለትዳር ነበር… ሚስቶችን መንፈሳዊ ኑሮአችሁን አሳዩ ሲል ባሎችን ደግሞ መራር አትሁኑባቸው ብሎአል።

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

II. ወንድነትና ሴትነት

- ወንድ የበላይ ሴትን የበታች አድርጎ ማሰብ (Chauvinism) እና ለሴቶች ከፍ ያለ መብትና ጥበቃን ስለማድረግ መቆም (Feminism)
- ወንድነት የሚሰማት ሴት እና ደካማ ወንድ
- ጸታን መቀየር

1. ወንድነት
   - የወንድነት መለኪያ ያልሆኑ ነገሮች
     1. ጨካኝ፣ ጨኸታም በጡንቻውና በድምጽ ማስፈራራት
     2. ስንፈተ ወሲብ
     3. ሌሎችን ልቆጣጠር ማለት
   - የሚሆናቸው ነገሮች
     1. ራስን መቆጣጠር
     2. ጀግና፡- አይጥ ሲያይ መውጫ ቀዳዳ የሚፈልግ መሆን አይጠበቅበትም...
     3. ትሑት

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

4. ርኅሩኅ
5. የሚገጥሙትን ነገሮች ተጋፍጦ የሚወጣ
6. በማኅበራዊ ሕይወቱ ጠንካራ የሆነ
7. እምነት የሚጣልበት
8. ኃላፊነት የሚሰማው
9. ቅን መሪ
10. የማይለዋወጥ ጽኑ አቋም ያለው
11. ወሳኝ ወይም በነገሮች ላይ መወሰን የሚችል
12. የማይነዋወጥ - የመጣ ነፋስ የሚያወዛውዘው ያልሆነ

2. ሴትነት

- የሴትነት መለኪያ ያልሆኑ ነገሮች
    1. መጥፎ ነገር እንዲሠራ አሳሳች መሆን
    2. የተምታታ ደካማነት፡- እንዲታዘንላቸው ደካማ መስሎ መታየት
    3. የወንዴነት ጠባይ፡- እንደ አማዞን ደሴት ሰዎች ሆኖ መገኘት፣ እኔ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ ወንድ ባል አያስፈልገኝም... ማለት
    4. ማወክ ወይም መበጥበጥ
    5. ጨካኝነት
    6. ጨቋኝታምነት

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

- ሴት የምትሆናቸው ነገሮች፡- ቅዱሳት አንስትን የሚመስሉላቸውን ሁሉ መያዝ ይገባል።

1. ንጽሕና
2. ቅድስና
3. ጥበበኛ
4. ትሕትናን የተላበሰች ውብ
5. ቅን
6. ጸጥተኛና ዝግ ያለች
7. ርኅሩኅ
8. አፍቃሪና ተግባቢ
9. እናትነት

III. ክርስቲያናዊ መሪነት

- ፈላጭ ቆራጭነት አምባ ገነንነት የሌለበት ነው።

1. እምነት የሚጣልበት (መግባባት፣ መረዳዳትና ሥራዎችን ተግባብቶ መከፋፈል)
2. ትዕግሥት ያለበት። "ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም።" ***ቀዳ ቆሮ 13:4።***
3. ያግዛል፣ ያበረታታል። "ወንድሞች ሆይ... ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤ ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ።" ***ቀዳ ተሰ 5:14።***

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

4. ጥበበኛና ማስተዋልን ገንዘብ ያደረገ ነው። “ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። ... ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል።... ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ።” ***ኤፌ 5:26-27፣ 30፣33።***
5. መጋቢ ተንከባካቢ ነው። ***ኤፌ 5:29።***
6. ንቁ ነው ለሁሉ ይጠነቀቃል፦ አእምሮውና አካሉ።
7. ታማኝነትና ትሕትናን የያዘ ነው።
8. መሥዋዕትነት አለበት። “ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ።” ***ኤፌ 5:25።***
9. መንፈሳዊ ነው። “በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።” ***ኤፌ 5:26-27።***
10. ራስን ዝቅ በማድረግ የሚያገለግል ነው። “እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።” ***ዮሐ 13:14***

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

IV. ራስን መስጠት ማለት

1. ክብር መስጠት
2. አድናቆት
3. መፍራት
4. ከፍ ማድረግ
5. ራስን መግዛት
6. ማመስገን
7. ማገዝ፡- ድልድይና የተሸከመውን ምሰሶ አስቡ... ምሰሶ ባይሸከመው ድልድይ አይቆምም፡፡ የምሰሶው መሰበር የድልድዩ መፍረስ ምንጭ ይሆናል፡፡ ምሰሶው ለድልድዩ ድልድዩም ለምሰሶው አስፈላጊ ናቸው፡፡
8. ማክበር
9. መስጠት
10. አብልጦ ማድነቅ ወዘተ ነው አንጂ ባርነት አይደለም፡፡

የወንድና የሴት ድርሻ - መሪነትና ራስን መስጠት

V. በቤተ ሰባዊ ሕይወት ውሳኔ ሰጪ ማነው?

- ክርስቲያናዊ ቤተ ሰቦች ሁለቱም ተማክረው ተስማምተው ይወስናሉ።
- ከባድና ቀላል ውሳኔዎችን መወሰን ቢያስፈልገን ወንዶች የትኛውን ትመርጣላችሁ? ሁለቱንም? ሴቶችስ? ሁለቱንም?
- እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የምንኖርና ትዳራችንም በክርስቲያናዊ ሥርዓት የሚመራ ከሆነ ባል ነኝና ብቻዬን ወሳኝ መሆን አለብኝ የሚል አይኖርም።
- መግባባት ስላልቻልን... እኔ ወንድ ስለሆንኩ እወስናለሁ... አይፈቀድም። በግድ ሚስቶቻችሁን አስጨንቃችሁ ብናደርገው እንኳ አንድ ቀን የሚያስከትለውን መጥፎ ውጤት እናጭዳለን።
- የእግዚአብሔር ዕቅዱ ሁለቱም ዋጋ ሥፍራ አላቸው የሚል ነው። ስለዚህ በትዳር ውሳኔ የሚወሰነው በሁለቱም (በባልና በሚስት) ስምምነት ነው።

For your quesries E-mail:
kesisolomon3@gmail.com

To get all lessons surf :
www.zeorthodox.org

... ክፍል ስድስት ይቀጥላል።

መስብሐት ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 6

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡ ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ግንቦት ፲፰ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

- በዛሬው ትምህርታችን አዲስ የሚጀመር ቤተሰባዊ ሕይወት እንዴት ሥርዓት እንደሚበጅለት እንማራለን፡፡
- ማንኛውም ቤተሰብ የሚተዳደርበት ሥርዓት ያስፈልገዋል፡፡
- ያለ ሥርዓትና ያለ መመሪያ የሚሄድ ቤተሰብ አቅጣጫውንና ግቡን ይስታል፡፡
- ስለዚህ ለገንዘባችን፣ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን፣ ለማኅበራዊ ሕይወታችነ፣ ለትምህርት፣ ለልጆች... እንዴት ሥርዓት እንደምናበጅለት እንማራለን፡፡
- ‹‹ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ፡፡ አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል፡፡ በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው፡፡ እውነተኛውን ሕይወት ይይዙ ዘንድ፥ ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ፥ መልካምን እንዲያደርጉ በበጎም ሥራ ባለ ጠጎች እንዲሆኑ፥ ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው፡፡›› *ቀዳ ጢሞ 6:10፣11፣17-19::*
- ለገንዘብ የምንሰጠው ዋጋ ገንዘብን ከመውደድ ይለያል፡፡ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው፡፡
- ባለጠግነትም ራስን ብቻ የሚያስደስቱበት ሆኖ በዚህ ዓለም የሚያልፍ ባለጠግነት እንዳይሆን መጽሐፍ ያስጠነቅቀናል፡፡
- ቅዱስ እንጦንስ የገዳማዊ ሕይወት መሥራች አባት ነው፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ‹‹ፍጹም ልትሆንስ ብትወድ ያለህን ሸጠህ ለድሆች ሰጥተህ ተከተለኝ...›› *ማቴ 19:21::* ያለውን የጌታችንን ቃል ሰማ፡፡ አባቱ ሲያርፍ የወረሰውን ለእህቱ የምትፈልገውን ሰጥቶ የተቀረውን ሁሉ ለድሆች ሰጥቶ ወደ አረፈው አባቱ አስከሬን ቀርቦ ‹‹ሁሉንም ያለፈቃድህ ትተህ ሄድህ፣ እኔ ግን በፈቃዴ ዓለምን እተወዋለሁ...›› ብሎ መነነ፡፡
- ወደዓለም የመጣነው ምንም ሳንይዝ ነው፡፡ ምንም ልንወስድም አይቻለንም፡፡ *ቀዳ ጢሞ 6:7-8::*

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

- ‹‹ ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና። የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ! ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም። ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን? ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው? ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት? እንግዲህ። ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል። ›› *ማቴ 6:19-34።*
- ለቤተሰባዊ ሕይወታችን የምናዘጋጀው ሥርዓት የሚመነጨው ከላይ ከተጠቀሰው የጌታችን ትምህርት ነው።
- ለትዳራችን የሚሆነውን ሥርዓት የምንዘረጋው የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት በሚቃረን መልኩ መሆን የለበትም። ለዚህ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን።

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

1. **ገንዘባችንን የምናስተዳድርበት ሥርዓት**
   1. ***ገንዘብና ፍቺ፦*** ዛሬ በርካታ ትዳር ይፈርሳል፤ አንዱ ምክንያትም የገንዘብ ጉዳይ ነው። መጽሐፋችን ለነገ አትጨነቁ ሲል በጀት አይኑራችሁ ማለቱ አይደለም።
   2. ***ገንዘብና ቅዱሳት መጻሕፍት ፦*** (2/3ኛው የምሳሌ መጻሕፍት ስለ ገንዘብ ይናገራሉ)።
      - ጌታችን በምሳሌ ካስተማራቸው ትምህርቶች 2/3ኛው ያህል ስለገንዘብና ስለበለጠግነት መሆኑ ስለምን ይመስለናል?
      - ገንዘብ ከእግዚአብሔር ለቤተሰቡ አካላት የተሰጠ ስጦታ ነው።
      - ከባልም ይምጣ ከሚስት የሚገባው ወደ አንድ ቋት ነው።
      - በብራችን ላይ ይህ ለባል ይህ ደግሞ ለሚስት ነው የሚል ተጽፎበት አናገኝም።
      - በባንክ ደብተራችን ላይ የተጻፍነው እኛ ብንሆንም ገንዘቡ የተሰጠን ከእግዚአብሔር ነው።
   3. ገንዘባችንን የምናስተዳድርባቸው ጠቃሚ ዘዴዎች (መንገዶች)
      I. ስለ ሀብት ዓለምና እግዚአብሔር የሚሉን ምንድር ነው? ዓለም የሌላውን ሰው ገንዘብ እንደልብህ ተጠቅሞ ባለጠጋ መሆንን (መኪና፣... መግዛት) ስትሰብክ በክርስትናው ደግሞ ባለጠግነት ልጅነታችን (ጥምቀት..) መሆኑንና ገንዘብም መጠቀሚያ ስጦታ እንደሆነ መረዳት።
      II. ገንዘብ ጋብቻን ደስታንና ሐሴትን የተሞላ እንዲሆን እንደማያደርገው ማወቅ።
      III. መንፈሳዊነትና የጋብቻ ሕይወት ገንዘብን የሚመለከቱበት መንገድ ተቀራራቢ መሆኑን መረዳት።
      IV. እግዚአብሔር ለጋብቻ የመረጠው ተቃራኒውን ነው። እኛ ገንዘቡን ለግጭት ... እንጠቀምበታለን፤ እርሱ ግን ባልና ሚስቱን ለማቀራረብ ለማግባባት እንደሚጠቀምበት ማወቅ።
      V. ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። ‹‹ወደ ዚህ ዓለም ስንመጣ ይዘን የመጣነው ምንም የለንምና ከዚህ ዓለም ስንወሰድም ይዘነው የምንሄደው የለም።››

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

1. **ገንዘባችንን የምናስተዳድርበት ሥርዓት...**

VI. እኛ የእግዚአብሔር ገንዘብ አስተዳዳሪዎች ወይም መጋቢዎች ነን። ገንዘቡንም የምናስተዳድረው እንደ እግዚአብሔር ዕቅድና ፈቃድ ነው።

- ‹‹ብልጥግናና ክብር በእኔ ዘንድ ነው፥ ብዙ ሀብትና ጽድቅም።›› ***ምሳሌ 8:18።***
- ‹‹ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?›› ብሎ የሚጠይቀን የሠተንን ገንዘቡን በአግባብ ለማስተዳደር አለመቻላችንን ሊገልጽልን ነው። ***ቀዳ ዮሐ 3:17።***

VII. በትዳር ወጪውን የሚመዘግብ፣ አውጥቶ የሚከፍል፣ እንደ በጀቱ እየተጠቀምን መሆኑን የሚከታተል አንድ ሰው ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜ ይኽን የሚሠሩት ሴቶች (ሚስቶች) ናቸው።

VIII. ገንዘቡ የእግዚአብሔር ነውና፡- በበጀቱ ውስጥ የሚያዙ ዝርዝር ነገሮች በባልና ሚስት መካከል ተገቢ ውይይትና ስምምነት ሊደረግባቸው ይገባል።

IX. ከጋብቻ በፊት፡-

I. ቢያንስ የእግዚአብሔርን ገንዘብ እንዴት እጅግ መልካም በሆነ መንገድ እንደምናስተዳድር መማር ይገባል።

II. ጋብቻችን የሚመራበትን ግባችንን፣ ዓላማችንን ደረጃ እናዘጋጅ፣ በየዓመቱ የተወሰኑ ቀናትን ወስደን እንገምግመው።

- ‹‹አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ።›› ዕብ 13፡5።
- ‹‹ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም።›› ***ካል ጴጥ 2:3።***

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

1. **ገንዘባችንን የምናስተዳድርበት ሥርዓት...**

X. እግዚአብሔር ገንዘብን

I. ታማኝነታችንን ለመመዘን

II. ፍቅሩን ለማሳየት

III. ተጋቢዎቹን በመወያየት የበለጠ እንዲቀራረቡ ለማድረግ ይጠቀምበታል።

XI. ተጋቢዎች እርስ በርስ መግባባት ሲሳናቸው እያንዳንዳቸው ከሁሉ የተሸለውንና ከሁሉ የባሰውን ሁኔታና ተስማምተው ሊኖሩበት የሚችሉት በምን እንደሆነ ይጻፉ።

XII. አንድ ከፍ ያለ ነገር ነገር ለመግዛት ከፈለጋችሁ ሦስት የዋጋ ማቅረቢያዎችን ወስዳችሁ ለአንድ ወር አቆዩት። ምክንያቱም ሌላ አስቀድሞ የሚያስፈልገን ነገር ተፈጥሮ የቀደመውን ነገር ላንገዛው እንችላለን።

XIII. በርካታ ሴቶች ወይም ሚስቶች ብዙ ገንዘብ አውጥተው መግዛት ሲፈልጉ የሚገዙት ልብስ ወይም ምግብ ሲሆን ወንዶች ደግሞ መኪና፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ ጀልባ ወይም አውሮፕላን ለየቅል መሆንን ማወቅ።

XIV. ብድርና የብድር ካርድ፦

<u>ይትበሃሎች፦</u>

I. ‹‹የግድ መበደር ይኖርብሃል።›› ይህን አባባል የፈጠሩት አይሁድ ናቸው። እነርሱ ግን ይህን አይጠቀሙበትም። በዚህች ምድር የኖሩ አያቶቻችን ፈጽመው ገንዘብ አልተበደሩም። ይልቁኑ ቆጥበው ከቆጠቡት ገዙበት እንጂ።

II. ‹‹የብድር ካርዳችንን በዘዴ እንጠቀምበት።›› እውነታው ያለሞኝነት መጠቀም ነው። ምክንያቱም ከኪሳችን ገንዘብ አውጥተን የምንገዛ ብንሆን እንጠነቀቃለን። የማንገዛውን ሁሉ ግን በብድር ካርዳችን እንገዛለን።

III. ‹‹ወለድ መክፈል ቀረጥን ለመክፈል አለመፈለግ ነው።›› ይህን የሚል እውነታ የለም።

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

በጀት

አገልግሎቱ ወይም ጥቅሙ፡-

- ተጋቢዎቹን ማቀራረብ
- እግዚአብሔርን ለመታመንና ትእዛዙንም ለማክበር
- ባወጣነው በጀት አጥር ዙሪያ ነጻነት ተሰምቶን በነጻነት እንድንንቀሳቀስ ነው።

- ስለ በጀታችሁ አብራችሁ ጸልዩ፣ በጀቱንም አብራችሁ አዘጋጁት።
- ከጋብቻ በፊት የአንድ ዓመት በጀታችንንና እቅዳችንን መሥራት ይኖርብናል።
- ከዕዳ የምንወጣበት የተሻለው መንገድ ተቃራኒውን ማከናወን ነው። ይህም ወደ ዕዳ ለመግባት ያደረግነውን ተቃራኒ ነገር መልሰን ብንፈጽም ከዕዳ ራሳችንን መገደብ እንችላለን።
- ገንዘባችንንም ሆነ ራሳችንን ለእግዚአብሔር እንስጥ። በመቀጠልም ላወጣነው ዕቅድ ተገዢ እንሁን። ዕቅዳችንን ከመተውም ሆነ ከመለወጥ እንቆጠብ።
- የሰማይ ወፎች ያለማቋረጥ ምግባቸውን ለማግኘት ወዲያና ወዲህ ይላሉ ይሠራሉ። ይሠራሉ እንጂ አይጨነቁም።
- ሰውም እየሠራ በገደቡ ሳይጨነቅ መኖር ይጠበቅበታል።
- ‹‹እጅግ ወይም ጥቂት ቢበላ የሠራተኛ እንቅልፍ ጣፋጭ ነው የባለጠጋ ጥጋብ ግን እንቅልፍን ይከለክለዋል።›› ***መክብብ 5:12።***
- ‹‹እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ባለጠግነትንና ሀብትን መስጠቱ፥ ከእርስዋም ይበላና እድል ፈንታውን ይወስድ ዘንድ በድካሙም ደስ ይለው ዘንድ ማሠልጠኑ ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።» ***መክብብ 5:19።***
- ‹‹እኔም እላችኋለሁ፥ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ፥ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ።› ***ሉቃ 16:9።***

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

በየወሩ በጀታችንን የምናስቀምጥባቸው አሥራ ሁለቱ መሳቢያዎች ወይም ፖስታዎች

1. አሥራት
2. ግብር ወይም ቀረጥ

   እኛ የምንጠቀምበት ገንዘብ የወሩ ጠቅላላ ገቢያችን አሥራትና ግብር ከተቀነሱለት በኋላ ያለው ገንዘብ ነው።
3. 30% ለቤት ዕዳችን፡- ለኢንሹራንስ፣ ግብር፣ ለመብራት ውሃ ለመሳሰሉትና ለጥገና
4. 15% ለመኪናችን ወይም ለመጓጓዣ፡- ለምዝገባዎች፣ ለነዳጅ፣ ለጥገና ወዘተ
5. 16% ለምግባችን
6. 5% ለቤተሰቡ አባላት ለሚሆን ልብስ
7. 5% ለኢንሹራንስ (ለሕይወት፣ ለጤና፣ ...)
8. 5% ለጤናችን ወጪ (ጥርስ፣ ሆስፒታል፣ መድኃኒቶች፣ ኮስሞቲክ ሰርጀሪ...)
9. 7% ለመዝናኛ (ከከተማ ወጥቶ ለመዝናናት፣ ዓለምን ለመጎብኘት... ከቤት ውጪ ለመመገብ...)
10. 7% ለሌሎች ጥቃቅን ወጪዎች (ሽቶ፣ ሻምፖ፣ ስጦታ ...)
11. 5% ለቁጠባ
12. 5% ዕዳን ለመክፈል።

- እርስ በርስ መግባባት ባይኖር ተስማምተን ወዳስቀመጥነው ተመልሰን ማስተካከልና ያላስቀመጥነውንና ያልተግባባንበትን ለይተን በማውጣት መተው ወይም መልሰን በመመካከር ማካተት ይገባናል።

የጋብቻ ሕይወታችን የሚመራበትን ሥርዓት ማዘጋጀት

2. ***መንፈሳዊ ሥርዓቶች***
    1. በየትኛይቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓታችን ይፈጸማል... በየትኛው አጥቢያ እናስቀድሳለን፣ ጉባኤ እንሳተፋለን፣ ልጆቻችን በየት እየተማሩ ያድጋሉ፣ የልጆቻችን የማይለወጡ ጓደኞቻቸው እነማን ናቸው?
    2. የንስሐ አባት፡- ባልም ሚስትም ሁለት አባት ሊኖራቸው ኤአችልም አንድ አባት እንጂ... በቤ/ክ ለምን ያህል ሰዓት አገልግሎት እንሰጣለን... በቤታችን የምናደርገው ጸሎት... የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት...
    3. ለጋብቻው የሚያስፈልግ መንፈሳዊ ምክር ከማን እንዴት እንቀበላለን? እነዚህ ሁሉ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል፡፡
    4. መንፈሳዊ መርሐ ግብሮቻችንም ሥርዓት ሊኖራቸው ያስፈልጋል፡፡
3. ***የማኅበራዊ ሕይወት ሥርዓቶች***
    1. ከአማኞቻችን ጋር የሚኖረን ግኑኝነት
    2. ዘመዶቻችንና ጓደኞቻችን
    3. የዕረፍት ጊዜያችን
    4. ከቤት ውጪ አብሮ መብላትና ቅዳሜና እሁድን አጠቃቀም ከበጀታችን ሳንወጣ ሥርዓት ያስፈልገዋል፡፡
4. ***ትምህርት፣ የተሻለ ዕድገት እና ሥራ***... ለማከናወን የተስማማንበት ሥርዓት ያስፈልጋል፡፡ ባል ሲማር ሚስት ነፍሰ ጡር ሆና ሥራም መሥራት ቢሳናትስ፣ ድንገት ከሥራ መሰናበት ቢኖርስ?... ተመካክረን ሥርዓት እናብጅለት፡፡
5. ***ልጆች***
    1. መቼ ልጆች እንዲኖረን እንሻለን? ሰቲቱ 32 ዓመት ሳይሆናት ባል ፒ ኤች ዲዬን ስጨርስ ቢልስ? ሥርዓት...
    2. ምን ያህል? 2፣ 4፣ 6፣ 8፣ ...? ተነጋገሩ ሥርዓት አድርጉለት፡፡
    3. እንዴት እናሳድጋቸው? ልጆችን እግዚአብሔርን እንዲፈሩ አድርገን ለማሳደግ የሚያስፈልገን ችሎታ ምንድን ነው? አስቀድማችሁ ተነጋገሩ ሥርዓት አድርጉለት፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons surf :

www.zeorthodox.org

... ክፍል ሰባት ይቀጥላል።

መስብሐት ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 7

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡ **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ግንቦት ፳፭ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

- ዛሬ በጣም ወሳኝ የሆነና ጥልቅ መንፈሳዊ መረዳትን የሚሻ አንድ ትምህርት እንማራለን።
- እርሱም መንፈሳዊ ሕይወትንና የሰውነት ፈቃድን መፈጸም የተመለከተ ነው።
- በጋብቻ ሕይወት መንፈሳዊነትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም ምን ዓይነት ተዛምዶ አላቸው?
- የሰውነት ፈቃድን መፈጸም አስመልክቶ ያለው የእግአብሔር እቅድና ግብ ምን እንደሆነም እንማራለን።
- በትዳር ሕይወት ስላለ የፈቃድ አፈጻጸም፣ መሰናክሎች፣ መንፈሳዊነትና የሰውነትን ፈቃድን በአግባቡ መፈጸምን የሚደግፉ ነጥቦችንም በእግዚአብሔር ፈቃድ እንመለከታለን።
- በተቀደሰው ትዳራችን የሚኖር መንፈስቀዱስ፣ የተስተካከለው መንፈሳዊ የሕይወት ደረጃችንና በትዳር ሕይወት ፈቃድን መፈጸም ስምምነት አላቸው።
- በተቀደሰ ጋብቻ የምንኖር ከሆንን በክርስቲያናዊ ጋብቻ በተፈቀደልን የሰውነት ፈቃድን የመፈጸም ሕይወት ታላቅ ደስታን ማግኘት እንችላለን።

1. *የእግዚአብሔር እቅድ*

- እግዚአብሔር ለትዳር ሕይወት ያለውን እቅድ አስመልክቶ ሦስት ነጥቦችን እንመለከታልን።

1. *ዘፍጥረት 1:26-28።*

- ‹‹እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።›

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

- ይህ የእግዚአብሔር እቅድ የመጀመሪያው ክፍል ነው።
- እግዚአብሔር መንፈስ ነው። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር በጋብቻችን ስለሚኖር መንፈሳዊ የሆነ የሰውነትን ፈቃድ የመፈጸም ሕይወት አስተምሮናል። ይህንንም ... ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት... በማለት ገልጦታል። -- ይህም ለሰው ዘር ሁሉ ጋብቻን አስመልክቶ የተሰጠ የመጀመሪያ ሕግ ነው።
- እግዚአብሔር ለሰው ዘር ያዘጋጀው እቅድ መብዛት ነው። ይህንም ለአዳምና ለሔዋን ነግሮአቸዋል። አባቶቻችን ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ ቅዱስ ቀሌምንጦስ እንደነገሩን ጋብቻቸውን በኤድን ገነት በቀደሰው ጊዜ አብሮአቸው በመሆን አረጋግጦላቸዋል። ***<u>ዘፍጥ 2:24።</u>***
- በኤድን ገነት ጋብቻን የመሠረተ እግዚአብሔር በገሊላ ቃና መልሶ በመባረክ ያረጋገጠው መሆኑን አባቶቻችን ነግረውናል።

2. <u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ።</u>

- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ « ተጠንቀቁ ! ተቀድሶ የተጀመረ ጋብቻ ንጹሕ፣ ቅዱስ ፣የተመረጠ፣ ምስጢር፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው፣ በፊቱም የከበረ መሆኑን እወቁ!» በማለት አስጠንቅቆናል።
- በመጀመሪያዎቹ አምስት ምዕተ ዓመታት የተቀደሰውን ጋብቻና ተራክቦንም የሚያራክሱ በርካታ የክህደት ትምህርቶች ይሰራጩ ነበር። በመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጉባኤ ሳይቀር ያገቡ ቀሳውስት እንዳይቀድሱ ለማድረግ ከመሞከር አንስቶ ብዙ የተሳሳቱ የክህደት ሥራዎች ተሠርተዋል። ይህ ጋብቻን አራክሶ የሚመለከት አመለካከት በዘመኑ በነበሩ አባቶቻችን ውድቅ ተደርጎ ነበር።
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በትምህርቱ የመራን ቀዳ ቆሮ 7፡3-5ን ወደ መመልከት ነበር።

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

3. ***ቀዳ ቆሮንቶስ 7:3-5::***

- ‹‹ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ:: ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ:: ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ::»
- ይህ ክፍል ቁጥር 3 በመጀመሪያ በትዳር ሕይወት ውስጥ ያለውን መፈላለግ (የሰውነት ፍላጎት) የሚመለከት ነው:: ቀጥሎም ቁጥር 4 ተራክቦን አስመልክቶ እያንዳንዳችን በሰውነታችን ላይ ያለንን ሥልጣን የሚያስረዳ ሲሆን ቁጥር 5 ደግሞ ተራክቦን አስመልክቶ እንዴት ራሳችንን ሥርዓት ማስያዝ እንዳለብን ያስረዳል:: ***<u>ተራክቦ</u>*** ማለት በትዳር ሕይወት የሰውነት ፈቃድን መፈጸም ማለት ነው::
- መስማማት ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ያህል ጊዜ? ሰይጣን በዚህ አጋጣሚ ሊጠቀምበት የሚችልበት ቀዳዳ አይኖረውም ይሆን? ሥርዓት እንዲኖረን ማድረግ ታላቁ መፍትሔ ነው::
- ይህ መልእክት የያዘው በዛሬው ትምህርታችን የምንዳስሰውን ዋና ዋና ነጥቦች ነው::
- ስለ መፈላለግ ወይም ስሜት ሲናገር መልዕክቱን የጀመረው ... ባል ለሚስቱ የሚያስፈልጋትን ያድርግላት በማለት... ባልን በመምከር ነው:: በተራክቦ ሴት ይህንን ናት::
- ባሎች ሆይ ለሚስቶቻችሁ የሚገባውን አድርጉ፣ ደስ አሰኙአቸው፣ እንዲረኩ አድርጉአቸው ነው የተባለው::

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

3. ***ቀዳ ቆሮንቶስ 7:3-5:...***

- እንዲሁ ሚስቶችም ለባሎቻቸው የሚገባውን ያድርጉላቸው አለ።
- ማንኛውም ሰው ከስሜትና በመፈላለግ የከሚኖረው ደረጃ ዘሎ ወደ አካላዊ ንክኪ ሊሄድ አይችልም። ምክንያቱም ሰዎች እንጂ እንስሳት አይደለንምና። ሰዎችም ብቻ ሳንሆን መንፈሳውያን ሰዎች ነንና።
- ስለምን በባል ጀመረ? ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ባል የሚመለከተውን ይህን ጉዳይ ይረሳልና ነው።
- ባል ሲሰጥ ሚስትም ደስ ተሰኝታ ትሰጣለች። ሁለቱም ክርስቶስ በቀደሰው ጋብቻ በተከበረው መኝታቸው በሰጣቸው በዚህ የተራክቦ ስጦታ ደስ ይሰኛሉ። ይህ የደስታ እንጂ የመሸማቀቅ ምንጭ አይደለም።
- ‹‹ መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን ›› ***ዕብ 13:4።***
- ወደ ቁጥር 4 ስንተላለፍ በተቀደሰው ጋብቻ ወደ ተከበረው መኝታችን ከመሄዳችን በፊት አልጋውን በትእምርተ መስቀል ምልክት እንባርከው። በመቀጠልም እግዚአብሔር ይባርከን ዘንድ አብረን ተያይዘን አባታችን ሆይ... ብለን እንጸልይ። በመጨረሻም እግዚአብሔርን ስላደረገልን ሁሉ እናመስግነው።
- ቁጥር 4 የሚጀምረው ... ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ ፤... በማለት በሚስት ነው። ምክንያቱም ለአንዳንድ ሴቶች አካላዊ ጉዳይ በጣም አስቸጋሪ ይሆንባቸዋልና ነው። ስለዚህ ሚስቶችን ተው ለማለት በእነርሱ ጀመረ። ... እንዲሁ ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። በማለትም ሥልጣኑ የጋራ እንደሆነ አስተማረን።
- እውነተኛው የሰውነታችን ባለቤት እግዚአብሔር ነው።
- በትዳር ባለ ተራክቦ ከቅድስና ወደ ቅድስና እንገባለን። የመጀመሪያው የትዳሩ መቀደስ ሲሆን ሁለተኛው በተቀደሰው ተረክቦ የሚገኘው ነው። ማንኛውም ነገራችን ንጹሕ ከሆነ ተራክቦው የበለጠ ቅዱስ ነው።

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

3. *ቀዳ ቆሮንቶስ 7:3-5:...*

- ይህም ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆኑ ዘንድ የሚያደርጉት ቀጥተኛ ግኑኝነት ነው። ሁለት ግማሽ ውሃ የያዙ ብርጭቆዎችን ውሃውን ከአንዱ ወደ አንዱ ስንገለብጥ እንደሚዋሐዱ አነድ ስለሆኑ፣ በየግላችን አይሆንም ለማለት ምንም ሥልጣን የለንም።
- አሳዛኙ ነገር ግን ከሚስቶች ይልቅ ከዚህ በፊት በዚህ የማይወቀሱት ባሎች አይሆንም ባይ ሆነው መገኘታቸው ነው። ዛሬ ዛሬ ምን እየሆነ እንደሆነ ማወቅ እየቸገረ ነው። ምንም ይሁን ምን ሥልጣኑ የጋራ ነው።
- ከሁለት አንዳቸው ታመው አንዳቸው ስለሌላው ሕመሙ ተሰምቶአቸው አይሆንም ይሉ እንደሆነ ነው እንጂ በባዶ ሜዳ በየግል አይሆንም ለማለት ለማንም አልተፈቀደም።
- ቁጥር 5 እንዴት ሥርዓት እንደምናሲዘው ... ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ ... በማለት ያስረዳናል።
- ለተወሰነ ጊዜ ለጸሎትም ይሁን ጊዜውን ለመንፈሳዊ ነገር ለመጠቀም ተነጋግረን ሌላው ወገን ተስማምቶ የንስሐ አባትን ምክር ተቀብሎ አብሮ ለመጸለይ ለመጾም ካልሆነ በቀር በግል ተነስቶ ማድረግ አልተፈቀደም።
- በመጨረሻ መንኩሶ ተራክቦን ትቶ ለመኖር እንኳ ለመወሰን ስምምነት ያስፈልጋል።
- ጾሙን ወይም ጸሎቱን ጀምረን በመካከሉ አንዳችሁ መፈተን ቢገጥም እርስ በርሳችሁ ተጋገዙ። ይህ ምንም ስህተት የለውም። ካልተቻላችሁ ተስማምታችሁ የተቻላችሁን አድርጉ።
- ከቅዱስ ቁርባን በፊት ለተወሰኑ ሰዓታት ስንጦም ዓይን፣ አእምሮአችን፣ ልባችን፣ ሆዳችን፣ ሰውነታችን ሁሉ መጾም አለበት። ምግቡ ንጹሕ ቢሆንም ከምግቡ ለተወሰነ ሰዓት እንጦማለን። ከተራክቦም ተስማምቶ እንዲሁ ሊሆን ይገባል።

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

2. የእግዚአብሔር ግቦች

I. አንድ መሆን

- ‹‹ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ።›› ማቴ 19:2-3።

II. መብዛት (ዘር መተካት)

- ይህ አንድነት በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምሕሮ ቢወልዱም ባይወልዱም ሳይለያዩ ለመኖር ነው።
- በአንዳንድ የእምነት ድርጅቶች አንድነት ለመውለድ ነው፤ ካልወለደች/ደ ይለያያሉ።

III. ደስ መሰኘት (በተራክቦና በመረዳዳት)

- እግዚአብሔር ይህን ግኑኝነት አስደሳች እንዲሆን አዘጋጅቶታል።
- እግዚአብሔር በሰጠን በዚህ የተቀደሰ ስጦታ ሁሉ ደስ መሰኘት አለብን።
- ‹‹ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር...» ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈልን። ቀዳ ጢሞ 6:19።
- እግዚአብሔር ያለበት ነገር ሁሉ አስደሳች ነው። ያለ ፍርሃት በግኑኝነታች ተደስተን እግዚአብሔርን አንተ በመካከላችን በመኖርህ ደስ ተሰኝተናል ብለን እናመስግነው።
- ለወንዱም ለሴትም የፈጠረው የተራክቦ አካላት የተፈጠሩት ለደስታና ዘር ለመተካት ምክንያት እንዲሆነን ነው።

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

3. ተራክቦ

- እግዚአብሔር ለሰው ያዘጋጀለት ይህ አካል አራት ደረጃዎች አሉት፡፡ ሴቶች በተራክቦ ጊዜ አራቱን ደረጃዎች ለማለፍ ረጅም ጊዜ ይወስድባቸዋል፡፡
- ሚስት ወደ ተራክቦ ከማለፍዋ በፊት በባልዋ ዘንድ ቁጥር አንድ ተመራጭ መሆንዋን ልብዋ ማረጋገጥ ይፈልጋል፡፡ በመቀጠል፣ በሰውነት ወደ መነካካት፣ ተራክቦ ወደማድረግ እያሉ የእፎይታ አየር እስከሚተነፍሱበት ተራራ መውጣት ይሻሉ፡፡
- ባሎች ግን በፓራሹት ከአየር እንደተወረወረ ሰው ወርደው የሚፈልጉበት ቦታ ማረፍና የእፎይታ ትንፋሻቸውንም ወዲያው መጨረስ ይችላሉና ከሚቸኩሉ ይልቅ መጠባበቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡
- ለተራክቦ የሚሆነው አካላችን የሚገኘው በመካከል ነው፡፡ በእግር መካከል አይደለም፡፡ ይህ በመካከል ያለ ሰውነታችን ከተቀደሰ መላው ሰውነታችንም የተቀደሰ ይሆናል፡፡
- ተራክቦ፡-
  - ጊዜ መስጠትን
  - ርኅራኄ መፈላለግ፣ በጎ ስሜት፣... ያለበት ፍቅርን
  - እርስ በርስ መናበብንና
  - ዋናውን ግብ አለመርሳትን ይሻል፡፡ ግቦቹም ከላይ በቁጥር ሁለት የተጠቀሱት ናቸው፡፡

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

4. የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች

- ሰይጣን ያገቡትንም ያላገቡትንም የሚዋጋው ቅድስናቸውን በመገናኛ ዘዴዎች፣ ልቅ የሆነ የወሲብ ፊልም በሚተላለፍባቸው መንገዶች ወይም ይህን በሚመስሉ መጻሕፍት፣ በኢንተርኔት፣ በቪዲዮ ፊልሞች፣... ነው።
- ከላይ ለተጠቀሱት ነገሮች መንገድ ያለን ጤናማ ያልሆነ አትኩሮት አእምሮአችንን ብቻ ሳይሆን ትዳራችንንም ሆነ ሕይወታችንን ሁሉ ያቆሸሸዋል።
- ይህ ተጽእኖ መላ ማንነታችንን ከሰው ጋር ያለንን ግኑኝነት ሳይቀር ያበላሻል።
- ልቅ የሆነ የወሲብ ፊልም በሚተላለፍባቸው መንገዶች (Pornography) የተጠመዱ ሰዎች የሚመለከቱት የራሳቸውን ፈቃድ ብቻ ነው። ከትዳር አጋራቸውም ጋር ፈቃዳቸውን ሲፈጽሙ አጋራቸውን ትተው በፊልም ያዩትን እያሰቡና እያሰላሰሉ ይፈጽማሉ። ይህም በአእምሮ የሚፈጸም ዝሙት ነው።
- ባሎች/ሚስቶች ሆይ ይህን የሚያደርጉ ካሉ አቁሙ! ልትሏቸው ይገባል። ይህ ቅድስና የተለየው ሕይወት ከትዳራችን ሊወጣ ይገባል ካላላችሁ ከፍያለ እንቅፋት በፊታችሁ ይጠብቃችኋል።
- ሌላ ሰው እያሰቡ ለሚፈጸም ድርጊት መሣሪያ አንሆንም፣ ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ለ Pornography አይደለም! ማለት ከኦርቶዶክሳውያን ተጋቢዎች ይጠበቃል።
- ካልሆነ ግን ይህ የዝሙት ዲያቢሎስ በትዳራችሁ ሆኖ ልጆቻችሁንም እንዲያጠቃ ትፈቅዱለታላችሁ።

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች ...

- ልጆቻችሁም በሰይጣን አሠራር ለመወሰዳቸውም በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ትሁናላችሁ።
- በPornography አመለካከቱ የተበላሸ ሰው በየትም ሥፍራ ባለው ግኑኝነት በሥጋ ፍትወት እጅግ የተቃጠለ ይሆናል። ቀልዱ፣ በሥራ ገበታው ከሚያገኛቸው ተቃራኒ ጸታዎች ጋር የሚኖረው አጋጣሚ ሁሉ በሥጋ ፍትወት እጅግ የተበረዘ ይሆናል።
- ዛሬ ማስታወቂያዎች ሁሉ በሥጋ ፍትወት እጅግ የተበረዙ ናቸው። ለምን? ሰው እየተሳበባቸው ስለሆነ፣ ሰው ወሲባዊ አእምሮ ይዞ የሚራመድ እየሆነ ስለመጣ ነው።
- ተራክቦ ሳያደርጉ መኖር እንደሚቻል እንመን። ሕይወታችን በሙሉ ግን የሥጋ ፍትወትን መፈጸም ከሆነ ያለርሱ መኖር ያቅተናል። ከዚህ ደረጃ የሚያደርሰንም ሰይጣን ነው።
- እግዚአብሔር ለትዳር ሁሉን አስተካክሎ ሠርቶታል። የሠራውም በፍጹም ቅዱስ ነው። ቤተ ክርስቲያን በተጋቢዎች መካከል የሚደረግን ግኑኝነት አስመልክቶ በፈጠረውና በፈቀደው መልክ ብቻ የሚፈጸመውን ታስተምራለች ትደግፋለች። ከዚያ ውጪ የሆነውን ግን ትቃወማለች።
- በቤተ ክርስቲያናችን በወንድም ሆነ በሴት በትክክለኛው የተራክቦ አካላቸው በኩል የማይፈጸም ግኑኝነት(አካለ ዘር ማደጉን መስፋቱን/መጥበቡን... ሳይቀር እየመረመሩ... አልፈው ወጥተው... የሚያደርጉትን ሁሉ) የእግዚአብሔር እቅድ እንዳልሆነ ታስተምራለች። በትዳር ያለ ግኑኝነት ደስታ የጋራ የሆነ ገጽታ ያለው ነውና።
- ከመሥመር በወጣ መንገድ የሚገኙ ወደ ማይወጡበት ከፍተኛ አደጋና ችግር ውስጥ ይወድቃሉ።

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች ...

- ወደ አንዱ የአካላችን ክፍል የገባ ኃጢአት በቀላሉ አይወጣም። የናርኮቲክ ሱስ ያለባቸው ሰዎች የወሲብ ሱስ ካለባቸው እጅግ የተሻሉ ናቸው፤ ምክንያቱም ችግራቸው በቀላሉ ሊወገድ ይችላልና።
- ጻድቁ ኢዮብ በሕይወቱ የወሰነው ከላይ የተጠቀሱትን አስመልክቶ የሚለን ትምህርት ሊሆነን ይገባል።
- ‹‹ ከዓይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገባሁ
  እንግዲህስ ቄንጆይቱን እንዴት እመለከታለሁ? የእግዚአብሔር እድል ፈንታ ከላይ፥
  ሁሉንም የሚችል አምላክ ርስት ከአርያም ምንድር ነው? መዓትስ ለኃጢአተኛ፥
  መለየትስ ለሚበድሉ አይደለምችን? መንገዴን አያይምን?
  እርምጃዬንስ ሁሉ አይቈጥርምን? በእውነተኛ ሚዛን ልመዘን፥
  እግዚአብሔርም ቅንነቴን ይወቅ።
  በሐሰት ሄጄ እንደ ሆነ
  እግሬም ለሽንገላ ቸኩላ እንደ ሆነ፥ እርምጃዬ ከመንገድ ፈቀቅ ብሎ፥
  ልቤም ዓይኔን ተከትሎ፥
  ነውርም ከእጄ ጋር ተጣብቆ እንደ ሆነ፥ እኔ ልዝራ፥ ሌላ ሰውም ይብላው
  የሚበቅለውም ሁሉ ይነቀል። ልቤ ወደ ሌላይቱ ሴት ጐምጅቶ እንደ ሆነ፥
  በባልንጀራዬም ደጅ አድብቼ እንደ ሆነ፥ ሚስቱ ለሌላ ሰው ትፍጭ፥
  ሌሎችም በእርስዋ ላይ ይጐንበሱ። ›› *መጽ ኢዮ 31:1-10።*

መንፈሳዊ ሕይወትና የሰውነትን ፈቃድ መፈጸም

የተቀደሰውን ጋብቻ ቅድስና የሚያቀጭጩ ምክንያቶች ...

- ሌላው አደናቃፊ ምክንያት ባሎች አስቀድሞ የዘር ፍሬዬ ይፈሳል ሲሉ፣ ሚስቶች ደግሞ በግኑኝነቱ የተነሳ እታመማለሁ፣ እቆስላለሁ ፊስቱላ ይሆንብኛል ብሎ ማሰብና መፍራት ነው።
- አንድንድ ዶክተሮችም ጠባብ ስለሆነ ዳይሌት መደረግ አለብሽ ብለው በአግባብ ወዳልተጠና ሴቶቹን ወደ ሚያስጨንቅ አቅጣጫ ይመራሉ።
- የልጅን ጭንቅላት የሚያክል ነገር የሚያስወጣ አካል የባልን የዘር አካል ማሳለፍ ይሳነዋል? ተረጋግተን እንራመድ ፍርሃቱም ሆነ ሕመሙ ያኔ ይርቅልናልና።
- በተጨማሪነት የምናነሳው አደናቃፊ ነገር ተራክቦን ለመፈጸም የሚያስችል ፍላጎት ማጣት ነው። በሥራ ጫና መብዛት የተነሳ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለተራክቦ ያላቸው ፍላጎት ተዛብቶባቸዋል። ለምሳሌ ለመጥቀስ ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ አገር የተደረገ ጥናት እንደጠቆመው 43% ክርስቲያኖች ሴቶችና 31% ያህል ክርስቲያኖች ወንዶች ከሥራ ጫና መብዛት የተነሳ ለተራክቦ ያላቸውን ፍላጎት አጥተው ተገኝተዋል።

የተቀደሰውን ጋብቻ የግኙኝነት ቅድሰና የሚያጠናክሩ ምክንያቶች

1. ጸሎት።
2. እርስ በርስ መግባባት ወይም መነጋገር
3. እገዛ ሲያስፈልገን እንዲደረግልን መጠየቅ
4. ምቹ ጊዜና ቦታን መምረጥ
5. ፈቃዳችንን ለመፈጸም ያለብንን ስንፈት በየጊዜው እያከሙ ማሻሻል። ለምሳሌ ስንፈት ያለባቸው አለብን ብለው ራሳቸውን ሳያሳምኑ በየጊዜው ከትዳር አጋራቸው ጋር በግልጽ እየተነጋገሩ ክፍተቶቻቸውን ማጥበብና የችግራቸውንም መፍትሔ በጋራ ፈልገው ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል።
6. በመካከል መቀዛቀዝ ካለ በዚህ ችግራችን ዙሪያ ምክር በማግኘት ማስተካከል
7. በትዳሩና በግኙኝነቱ ፍቅር እንዲሰለጥን በእግዚአብሔር ግብ መመራት። እነርሱም አንድነትን መጠበቅ፣ በተሰጠን የትዳር ስጦታ ማመስገንና በትዳሩ ደስታን ማግኘት ናቸው።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org

... ክፍል ስምንት ይቀጥላል።

መስብሐት ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ታሪክ - ክፍል 8

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡ **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሰኔ ፪ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

ቁጣና የቤት ውስጥ ጥቃት

- ዛሬ ሁላችንንም የሚመለከት አንድ ርዕሰ ጉዳይ እንመለከታለን። እርሱም ቁጣንና የቤት ውስጥ ጥቃትን የተመለከተ ነው።
- እስከዛሬ ድረስ በሕይወቱ ሳይቆጣ የኖረን ሰው ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው።
- ቁጣ በተለያየ ምክንያት የሚከሰት ሲሆን ተቆጪነትም የተለያዩ ጉዳዮችን ጠቋሚ ነው።
- ጌታችን ቁጣን ከመግደል ጋር በማነጻጸር ገልጦታል። በብሉይ ዘመን የነበረውን የመግደልን ድርጊት ከቁጣ ጋር በሐዲስ አነጻጽሮታል።
- *ማቴ 5:21-26።*
- ‹‹ለቀደሙት። አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል። እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ። አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤ እውነት እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።›
- በብሉይ የሚገድል ሁሉ ይገደል ነበር።
- አንድ ሰው በውስጡ ሸምቆ በወንድሙ የሚቆጣ ከሆነ ይፈረድበታል። እንዲህ ያለውን ሰው ውስጡን እግዚአብሔር እንጂ ሰው ሊያነበው አይችልም።
- እግዚአብሔር እንደ ዝሙት ሁሉ መግደልንም ሆነ ቁጣን መርምሮ የሚመለከተው ከልባችንና ከአእምሮአችን ነው። መርምሮ አይቶንም እንደሥራችን ይፈርዳል።

ቁጣና የቤት ውስጥ ጥቃት

- በተጨማሪም በርዕሳችን ዙሪያ ትዳርን አስመልክቶ በጣም አስፈላጊ የሆነውን መልዕክት እንመልከት።
- *ኤፌሶን 4:26-27 እና 31-32።*
- ‹‹ ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት። ... መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ። እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።››
- ባልተግባባችሁበት ጉዳይ የተነሳ በመካከላችሁ ቁጣ ቢኖር ቁጣችሁን አብርዳችሁ አብራችሁ ለጸሎት በመቆም እስክትጸልዩ ድረስ እንደተቆጣችሁ ወደ መኝታችሁ አትሂዱ።
- በርግጥ አድራችሁ የምትፈቱበት ሥርዓት ኖሮአችሁ ተስማምታችሁ ከሆነ መልካም ቢሆንም እያሰላሰላችሁት ግን ወደ መኝታችሁ አትሂዱ።
- ምክንያቱም ከቁጣው ጋር ዲያቢሎስ ይኖራልና ነው። በሌላው ተቆጥቶ ይቅር ይል ዘንድ ያቃተው ሰው እንቅልፍ እንዴት አድርጎ ይወስደዋል? ይቅር አለማለታችን ራሱ ይቀሰቅሰናል።
- ይቅር ማለት አለመቻል በስጋት የተሞላንና የታወክን ያደርገናል።
- ስለዚህ ለመነጋገር የምንችልበት ጊዜ እንኳ ብናጣ ተቆጥተን ከመተኛት ይልቅ ከጌታችን የተማርነውን ይቅርታን አድርገን እናንቀላፋ።
- ስለዚህ ዛሬ በአጭሩ ቁጣንና የቤት ውስጥ

ለቁጣ የሚያነሳሱን ምክንያቶች

1. ደህንነታችንና ጥበቃችን የተነካ የተደፈርን ወይም የተጎዳን መሆን
   - ‹‹ይህን የምትመኪበትን መልክ አጠፋዋለሁ... ›› እያሉ መዛት...
   - አንዳንድ ጊዜ በከረረ ንግግር ውስጥ ‹‹እገልሃለሁ... እገልሻለሁ ...›› ልንል እንችላለን። ይህ ዛቻ ለመግደል መሞከር፣ ወንጀልም ነው፤ ወደ ፍርድ ቤት ሊያስቀርበን ይችላል፤ በክርስትናም አልተፈቀደም።
   - ስለዚህ የሌሎች ጸጥታና ደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን አንደበታችንን/ምላሳችንን መጠበቅ ይገባናል።
2. መብትን መጣስና ግጭት
   - መብትን መጣስ በሂደት ቁጣን ያስከትላል።
   - አንዳንዴ ሳይታሰብ ይፈነዳል። ያም ነውጠኛነትን ሁከትን ያስከትላል።
3. ሰውን መናቅ ወይም ማቃለል
4. ማስፈራራት፣ ማስደንገጥ፣ ግትርነት
5. የሰውን መብት መጣስ፦ በትዳር ባልም ሚስትም መብት ያላቸው ቢሆኑም አንዱ የላለውን አለማክበሩ።
6. ጥብቅ ሥርዓትን/መመሪያን እሴቶችን መጣስ
   - የያዕቆብ ልጆች ጥብቅ ሥርዓታቸው/መመሪያቸውና እሴቶቻቸው ተጥሰው እህታቸው ዲና በተነካች ጊዜ ያ ሰው የሚያገባት ቢሆንም እንኳ ወንድሞችዋ ያደረጉትን እናስታውሳለን? ያገኙትን ሁሉ ገደሉ ይላል ቅዱስ መጽሐፍ...
   - በክርስቲያኖች ወይም በሕዝብ ዘንድ የታመነበትን መልካም ነገር የሚጥስ ሲገጥመን እንቆጣለን።
   - ቅድስና የተለየውን ድርጊት የሚያስፋፋንም ሰው እንቃወማለን። ድርጊቱንም ለማውገዝ ራሳችንን ዋና ተዋናይ እናደርጋለን።
   - እንዲህ ያለውን ነውር ነገር ከሚቃወሙም ጋር አንድነት ፈጥረን እንቆማለን ጥብቅ ሥርዓትንመመሪያና እሴት ተጥሶአልና።

ለቁጣ የሚያነሳሱን ምክንያቶች

7. ያልተሟላ ፍላጎት
    - አንድን ልጅ ያለአግባብ ዛሬ ምግብ አትበላም ብለን ብንከለክለው መቆጣቱ አይቀርም...
8. ለረጅም ጊዜ ያልተፈቱ ችግሮች
    - መለያየት፣ ፍቺ፣ ግኑኝነትን ማቋረጥ፣ ኃጢአት፣...
9. የአደንዛዥ እፅ ሱሰኝነት
10. የሰውነታችን ችግሮች፡- እንቅርት፣ የጭንቅላት እጢ... ቁጣን ያባብሳል።

- ከላይ የተጠቀሱትም ሆኑ ሌሎችም በርካታ ምክንያቶች ለቁጣ ምንጭ ናቸው።
- አሁንም ሆነ ከዛሬ በፊት ለቁጣ ምክንያት የሆኑንን ምክንያቶች እያንዳንዳችን እንፈልግ።

ቁጣን መግለጫ መንገዶች ወይም የቁጣ ዓይነቶች

1. ከማፈር፣ ከፍርሃት ወዘተ የተነሳ ነገሮች ለመሸፋፈን መሞከር ወይም ስንሞክር የምንቆጣው ቁጣ
2. ያበጠ ነገር ሲፈነዳ የሚከሰት፡- የት፣ መቼ፣ እንዴት፣ ... ተናደድን? ማታ ደክመን ሳለ፣ የትዳር አጋራችንን ስናይ? ስንናደድስ ትንፋሽ ያጥረናል? ደም ሥራችን ይወጠራል? ጀርባችንን ያመናል?
3. አሁን ወይም ከዚህ በፊት በሆኑ ነገሮች በሌሎች መናደድ
4. በራስ መቆጣት ወይም መናደድ
5. በእግዚአብሔር መቆጣት ወይም መናደድ

የቁጣ ማከሚያ መንገዶች

1. የመቆጣት ወይም ቶሎ የመናደድ ችግር እንዳለብን አምነን መቀበል
2. የተናደድንባቸውን አጋጣሚዎች በማስታወስ የት፣ መቼ፣... ከማን ጋር ሁኔታችን ምን ይመስል እንደነበር ራሳችንን እናስታውስ
3. ራስን መቆጣጠር
    - ከቦታው ቶሎ ርቆ መሄድ
    - ተናደን ምንም ነገር ቶሎ ከመናገር አፋችንን መቆጠብ
    - ተናደን መኪና አለመንዳት ከሆነም ቀስ ብለን ማሽከርከር፣ እናንብብ፣ ... በአንድ ጉዳይ ራሳችንን እንጥመድ
4. ለምን እንደተናደድን እንግለጽ
5. ሊረዱን የሚችሉ መካሪዎች እንዲመክሩን ማድረግ
6. ይቅር ማለት
    - ይቅር ካልን ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ሰጠን ማለት ስለሆነ አንጨቃጨቅ፣
    - ጌታችን በመስቀል ሆኖ ተቸንክሮ .. የሚያደርጉትን አያውቁምና ብሎ ይቅር እንዳለን እናስብ።
7. በመንፈሳዊ ጎዳና የሚመሩን እንዲኖሩን መሆን
    - የንስሐ አባታችን ምክር ዘወትር የማይለየን እንሁን

የቤት ውስጥ ጥቃትና ግጭት

1. የመቆጣት ወይም ቶሎ የመናደድ ችግር እንዳለብን አምነን መቀበል
2. የተናደድንባቸውን አጋጣሚዎች በማስታወስ የት፣ መቼ፣... ከማን ጋር ሁኔታችን ምን ይመስል እንደነበር ራሳችንን እናስታውስ
3. ራስን መቆጣጠር
    - ከቦታው ቶሎ ርቆ መሄድ
    - ተናደን ምንም ነገር ቶሎ ከመናገር አፋችንን መቆጠብ
    - ተናደን መኪና አለመንዳት ከሆነም ቀስ ብለን ማሽከርከር፣ እናንብብ፣ ... በአንድ ጉዳይ ራሳችንን እንጥመድ
4. ለምን እንደተናደድን እንግለጽ
5. ሊረዱን የሚችሉ መካሪዎች እንዲመክሩን ማድረግ
6. ይቅር ማለት
    - ይቅር ካልን ጉዳዩን ለእግዚአብሔር ሰጠን ማለት ስለሆነ አንጨቃጨቅ፣
    - ጌታችን በመስቀል ሆኖ ተቸንክሮ .. የሚያደርጉትን አያውቁምና ብሎ ይቅር እንዳለን እናስብ።
7. በመንፈሳዊ ጎዳና የሚመሩን እንዲኖሩን መሆን
    - የንስሐ አባታችን ምክር ዘወትር የማይለየን እንሁን

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org

... ክፍል ዘጠኝ ይቀጥላል።

መስብሐት ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ቅድመ ጋብቻ

ክፍል 9

የጋብቻ ዓላማ ምንድር ነው ፤ ሥርዓተ ተክሊል ለማን ይፈጸማል ፤ ከጋብቻ አስቀድሞ መታወቅ የሚገባቸው ጉዳዮች ምንድር ናቸው?

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
ሰኔ ፲ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

ቅዱስ ጋብቻ

የጋብቻ ዓላማ

ሥርዓተ ተክሊል ለማን ይፈጸማል?

የተለያዩ መታወቅ የሚገባቸው ጉዳዮች

የጋብቻ ዓላማ

ለመረዳዳት

- ዘፍጥረት 2 * 20 እና መክብብ 4 * 9 — 11

ዘር ለመተካት

- ዘፍጥረት 1 * 25 እና መዝሙር 126 * 3

ከፍትወት ወይም ከዝሙት ለመጠበቅ

- 1ኛ ቆሮ 7 * 8 - 9 ፣ 1ኛ ቆሮ 5 * 1 ፣ ምሳሌ 6 * 30 — 32

የጋብቻ ሕግጋት

1. ከተጋቡ በኋላ አንድ አካል ናቸው። ማቴ 19 * 4 — 6
2. መፋታት ክልክል ነው። ሚል 2 * 14
3. አንድ ወንድ ለአንድ ሴት። 1ኛ ቆሮ 7 * 2
4. የሚገባቸውን ሁሉ መጠበቅና ማድረግ። 1ኛ ቆሮ 7 * 3
5. ባልም ሚስትም በራሳቸው ሥልጣን የላቸውም። 1ኛ ቆሮ 7 * 4
6. ኃላፊነትን መወጣት። ኤፌ 5 * 20 — 23 ፤ ቆላ 3 * 18 -19።
7. ለጾምና ለጸሎት ካልሆነ አለመለያየት። 1ኛ ቆሮ 7 * 5
8. ሥጋዊ ጌጥ አለማብዛት። 1ኛ ጴጥ 3 * 1 - 4
9. ድንገተኛ ግጭት ቢከሰት ወዲያው መታረቅ። 1ኛ ቆሮ 7 * 10-11
10. በሞት ካልሆነ አለመለያየት። 1ኛ ቆሮ 7 * 39 እና ሮሜ 7 * 2 -3
11. ከሥጋዊ፤ መንፈሳዊ፤ የጋብቻ ዘመድ አለማግባት።

    ዘሌ 18 * 6-20፤ ዘሌ 20 * 16-21፤ ማር 6 * 17።

የጋብቻ ሕግጋት የቀጠለ...

1. ልጅ በሥጋ ዝምድና የሚከተሉትን አያገባም::
   - የቅድመ አያቱን እናት፤ እህት፤ ሚስት፤ ልጅ
   - የአያቱን እናት፤ እህት፤ ሚስት፤ ልጅ
   - የአባቱን እናት፤ እህት፤ ሚስት፤ ልጅ
2. አባት በሥጋ ዝምድና የሚከተሉትን አያገባም::
   - የሴት ልጁን፤ የልጅ ልጁን፤የልጅ ልጁን ልጅ
   - የወንድ ልጁን ሚስት፤ የሚስቱንም አያት ፣ እናት ፣ እህት ፣ ልጅ
   - የልጅ ልጁን ሚስት፤ የሚስቱንም አያት ፣ እናት ፣ እህት ፣ ልጅ
   - የልጅ ልጁን ልጅ ሚስት፤ የሚስቱንም አያት ፣ እናት ፣ እህት ፣ ልጅ ::
3. በጋብቻ ዝምድና ባል/ሚስት የሚከተሉትን አያገቡም::
   - የሚስቱን አያት፣ እናት ፣ አክስት ፣ እህት ፣ ልጅዋን ፣ የልጅ ልጇን
4. በመንፈሳዊ ዝምድና
   - <u>የክርስትና ልጅ</u> የክርስትና አባቱን ሚስት፣ እህት፣ ልጁን፣ የልጅ ልጁን
   - የክርስትና አባት የክርስትና ልጁን እናት፣ እህት፣ ሚስት፣ ልጅ፣ የእህቱንና የወንድሙን ልጅ አያገቡም::

- በሃይማኖት አንድ ያልሆኑ አይጋቡም::
- መፋታት ባይፈቀድም ፍቺ በዝሙት (ሥጋዊና መንፈሳዊ) የተነሳ ሊከሰት ይችላል::
- ሌላ ማግባት የሚቻለውም በዝሙት ፍቺና በሞት የተነሳ ብቻ ነው::

ተክሊል የሚገባው ለማን ነው?

1. ሥጋዊ ድንግልና ላላቸው:: ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 906
   - በሕክምና የተነሣ ድንግልናቸውን ያጡ
   - በተፈጥሮ ሲወለዱ የድንግልና ምልክት የሌላቸው
   - ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ ተገደው የተደፈሩ
   - ከአቅም በላይ የሆነ ሥራ በመሥራት ድንግልናቸውን ያጡም አይከለከሉም::

2. የሃይማኖት አንድነት ላላቸው:: 2ኛ ቆሮ 6 * 14 - 18

3. ከ 20 በላይ የሆነ ወንድና ከ15 ዓመት በላይ ለሆነች ሴት::
   ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 883-884 እና አንቀጽ 24 * 894

4. ፈቃደኝነታቸውን ለገለጹ ተጋቢዎች:: ፍ. ነገ. አንቀጽ 24 * 906

ጸሎተ ተክሊል ከቅዳሴ በፊት የሚፈጸም ሲሆን ያለ ሥጋ ወደሙም አይፈጸምም::

ከላይ የተጠቀሱትን ማሟላት ያልተቻላቸው ተጋቢዎች በሙሉ ጸሎተ ንስሐ ወይም ፍትሐት ዘወልድ ተነቦላቸው ቅዱስ ቁርባን ተቀብለው ኑሮአቸውን ይጀምራሉ::

መተጫጨት

በመተጫጨት ሂደት በወንዶች የሚፈጸም ስህተት

1. የሌለን ሀብት፤ ማዕረግ አለኝ ማለት

2. ደመወዝን ከፍ አድርጎ መናገር

3. ከጋብቻ በፊት ፈቃደ ሥጋን ለመፈጸም መፈለግ

4. አንድ ለአንድ ብቻ መፈቀዱን እያወቁ ብዙ ሴቶችን መከጀል

5. ከእውነተኛ ፍቅር ይልቅ በገንዘብ ለመግዛትና ለመቆጣጠር ማሰብ

6. ራስን ንጹሕ አድርጎ ሌላውን ሰው ማማትና ወዘተ... በዚህም የተነሳ እውነቱ ሲታወቅ አመኔታ ይጠፋል ጭቅጭቅ ይነግሳል።

መተጫጨት የቀጠለ...

በመተጫጨት ሂደት በሴቶች የሚፈጸም ስህተት

1. ፍቅርን ሳይሆን ገንዘብና ሀብትን ብቻ መመልከት

2. ክፉ ባልንጀሮችን በመከተል ለዝሙትና በአለባበስም ምቹ ላልሆነ ሕይወት መጋለጥ

3. የተለያየየ ወንዶችን በእጮኝነት ማቅረብና ዕድሜን መጨረስ

4. ከተዋወቁት ሁሉ ወንድ ጋር መላፋት::

ሴቶች ሆይ:- መተጫጨት ማለት መጋባት ማለት ስላልሆነ የሁለት ደቂቃ ቀልድ የአንድ ሰዓት ልፊያ አስከትሎ ይኽም ልፊያ የማይጠፋ ጸጸት እንዳያተርፍ መጠንቀቅ ተገቢ ነው::

በትዳር ጓደኛ ምርጫ ስኬታማ ለመሆን

1. መንፈሳዊ ሕይወትን አስተካክሎ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ።

2. እውነተኛ መሆን - ለማግኘት ስንል የሌለንን አለን አለማለት።

3. አንድ ወጥ ጠባይ ያለን መሆን፡- የምንውልበትን ቦታ፤
   የምናበጃቸውን ጓደኞች፤ አነጋገራችንንና አካሄዳችንን መወሰን።

4. በዓላማና በአስተሳሰብ አንድነት መቀራረብ

5. የአንድ ሃይማኖት ተከታይ መሆን

6. የንስሐ አባቶችን ምክርና መመሪያ መከተል።

ቃል ኪዳን

ጽኑእ የፈቃድ ውል። እውነተኛነቱንም ለማረጋገጥ በእግዚአብሔር ስም ቀለበት በማሰር ይፈጸማል።

ቀለበት፡-

ክብነቱ፡- ጋብቻው መፋታት የሌለበት መጨረሻ የሌለው መሆኑን ማመልከቻ ሲሆን

የፍቅር ምልክት ነው። #እንደ ቀለበት በልብህ አኑረኝ; መኃ. 8 * 6

በአጠቃላይ የቃልኪዳን ምልክት ነው።

#አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ እርሱንም አምልክ በስሙም ማል።; ዘዳግም 6 * 13።

#በስሜም በሐሰት አትማሉ፥ የአምላካችሁንም ስም አታርክሱ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።;
ዘሌዋውያን 19 * 12

በአጠቃላይ ከጋብቻ በፊት ምን እናድርግ?

1. በፈሪሐ እግዚአብሔር ለመመላለስ መወሰን

#በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ቅን የሆነውን ነገር ስታደርግ ለአንተ ከአንተም በኋላ ለልጆችህ ለዘላለም መልካም ይሆንላችሁ ዘንድ እኔ የማዝዝህን እነዚህን ቃሎች ሁሉ ሰምተህ ጠብቅ። ; ዘዳግም 12 * 29።

2. በንስሐ ሕይወት ተጠብቆ መኖር።

ራእይ 3 * 19።

3. የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት መጠየቅ።

ትንቢተ ዮናስ ምዕራፍ 1 እና 2።

4. የአካልና የአእምሮ እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ብስለት ያለን መሆናችንን መመዘን። 1ኛ ቆሮ 13 * 11፣ 2ኛ ጴጥ 1 * 5 -10

5. ራሳችንን መቻል። ዘፍ 18 * 14፣ ዘፍ 3 * 17 ፣ 2ኛ ተሰ 3 * 10 – 12

የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ይታወቃል?

1. ማመንና መወላወል በሌለበት ፍቅር

2. እየጠወለገ ሳይሆን እየለመለመ በሚሄድ ግኑኝነት

3. ፈተና ሲያጋጥም ሳይሸነፉ በትዕግሥት በጋራ በመወጣት

ዮሐንስ 4 ፡ 18

ልናውቃቸው የሚገቡን

1. በድንግልና ለመኖር ወስኖ ቃልኪዳኑን ትቶ የሚያገባ ቃል ኪዳኑን አፍርሷልና ጸሎተ ተክሊል ሳይፈጽሙለት በቁርባን ብቻ ማጋባት የተፈቀደ መሆኑን። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 * 834 ፣ ዘጉ 30 * 2

2. ሚስት ስትጸንስና ከወለደች በኋላ ለተወሰኑ ቀናት ግኙኝነት አለማድረግ። ፍትሐ ነገሥት አ. 24 * 838፣ ዘሌዋ 20 * 18

3. ጃንደረባ ለሆነ ሰው፣ አእምሮ ለጎደለውም እብድ ሰው ሥርዓተ ተክሊል ፈጽሞ ማጋባት አይገባም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 * 857

4. የሚያገቡ ከሆነ፡- ባል ሚስቱ ስትሞትበት ከአንድ ዓመት በኋላ ሚስትም ባሏ ከሞተ ከ10 ወር በኋላ ከሐዘናቸው ተጽናንተው ያግቡ። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 * 916

5. ዘርን ከሴት ማኅፀን አውጥቶ በውጪ ማፍሰስ በደል ነው። ዘፍጥ 38 * 9-11

የጋብቻ ፍቺ

መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

E-mail: kesisolomon4@gmail.com

ቦታ፡ **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

ሰኔ ፲ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.

ጋብቻና ፍቺ

- “እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።” በማለት ሰው በፈትነትም ለብቻው መኖር የማይገባው መሆኑን ገልጦልናል። ዘፍጥ 2፡18።

- በአዳምን በሔዋን በደል ምክንያት የተበደለውንም ጋብቻ አምላካችን በመዋዕለ ሥጋዌው የመጀመሪያውን ተአምር ለጋብቻ በማድረግ ጋብቻን ወደ ነበረበት ክብሩ መልሶታል። ዮሐ 2፡1-11። በዚህም ጌታችን ጋብቻን የሰው የተቀደሰ ሕይወት አድርጎ ባርኮታል። የውሃውም ወደ ወይን መለወጥ በምድር በምትገኘው ቤተ ክርስቲያናችን በሚፈጸመው የጋብቻ ምስጢር ተጋቢዎቹ ከተራ ሰውነት መንፈሳዊ ሕይወት ያላቸውና በምድር ሆነው ሰማያዊ ሕይወት የሚመሩ ወደ መሆን የሚለውጣቸው መሆኑን የሚተረጉም ነው።

- በጋብቻው ለሚኖሩ ባልና ሚስትም ጋብቻቸውን የሚመሩበት ሕግና መመሪያ “ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ .... ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ” በማለት ሰጥቷል። ኤፌ 5፡22-29። ይህን የመሰሉ የጋብቻ ሕጎች ሲጣሱ ግን ጋብቻው ይፈርሳል።

- በክርስትና ትምህርት ጋብቻ ሊፈርስ የሚችለው በዝሙት ምክንያትነት ብቻ ነው። “እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።” እንዳለው። *ማቴ 19፡9፤ ዘሌዋ 18፡8-21፤ ዘጎ 5፡12፤ ዘዳግ 5፡21፤ ዘዳግ 22፡13-29፤ ሚል 2፡1-17።*

ትዳርን የሚጎዱት ምንድር ናቸው?

ዛሬ ለሚታዩት ከፍተኛ የጋብቻ ፍቺዎች ተጠቃሽ ምክንያቶች ምንድር ናቸው?

- ከአቅም በላይ በሆኑ ሆኔታዎች መወጠርና የሰውነት መዛል ወይም መድከም
    - በተለይ ሞያዊ እውቀታቸውን ለማስፋት ትምህርት ቤት የሚገቡ ወጣቶችንም ጭምር የሚመለከት በዚህ ሁኔታ ላይ ትኩረት ማድረግ አለብን::
    - በአንድ ወቅት ኮሌጅ መግባት፤ በመደበኛና በትርፍ ሰዓቶች መሥራት፤ ልጅ ወልዶ ማሳደግ፤ ቤት መሥራት ወይም መግዛት፤ ንግድ መጀመርን በጠቅላላው በአንድ ጊዜ ለማከናወን መሞከር የለብንም::

- ከአቅም በላይ በዕዳ ወይም በብድር መወጠርና ገንዘባችንንም እንዴ መጠቀም እንዳለብን ባለመስማማት የተነሳ የሚፈጠሩ ግጭቶች::

- ራስ ወዳድነት:- የዓለማችን ሰዎች ሁለት ዓይነት ናቸው:: እነርሱም ሰጪና ተቀባይ ይባላሉ:: በሁለት ሰጪዎች መካከል የሚኖር ጋብቻ መልካም ወይም ውብ ነው:: በሰጪና በተቀባይ መካከል ግን ግጭቶች መኖራቸው የማይቀር ነው::
    - ሁለቱም ተቀባዮች ከሆኑ በተወሰኑ ሳምንታት ውስጥ ይለያያሉ::
    - ራስ ወዳድነት ትዳርን ፈጽሞ የሚጠላ፤ የተሰለቸና ተጋቢዎቹ ሊኖሩበት የማይፈልጉት እንዲሆኑ ያደርጋል::

- ከጋብቻ ዘመዶች ጋር የሚኖር ጤናማ ያልሆነ ግኑኝነት

- ሊጨበጥ የማይችል ግምት፤ አንዱ ሌላውን ፋታ መንሳቱ፤ ሌላ መመኘት (መፈለግ)

- የሴቶች ለመውለድ አለመቻልና የረጅም ዓመታት ሕመም

ዛሬ ለሚታዩት ለፍተኛ የጋብቻ ፍቺዎች ተጠቃሽ ምክንያቶች ምንድር ናቸው?

- የገቢ ምንጮች መቋረጥ፤ የንግድ ተቋሞች መክሰር...
- በንግድ ውጤታማ ወይም ስኬታማ መሆን
- ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ ጋብቻን መፈጸም
    - ከ14 እስከ 17 ዓመት ባለው ዕድሜ ውስጥ ሆነው የሚያገቡ ልጃገረዶች ለአቅመ ሔዋን ደርሰው ከሚያገቡ ልጃገረዶች በእጥፍ ከፍያለ ፍቺ ያጋጥማቸዋል።
    - የጉርምስና ጊዜ አፍላ ስሜትና ለጋብቻ ዕድሜ ሳይደርሱ ማግባት ከፍተኛ ጫናና ትርምስ በመፍጠር ተጋግዘው በአጭሩ የትዳርን ዕድሜ ይቀጫሉ።
    - አስቀድሞ ጉርምስናን በመጨረስ ወደ ጋብቻ መድረስ ተገቢና ብቸኛ መንገድ ነው
- አልኮል መጠጦችን ማዘውተርና ስካር
- ልቅ የወሲብ ፊልሞችን መመልከት፤ ቁማር፤ እና ሌሎችም ሱሶች
- አደንዛዥ እጾችን (ጫት፤ ሺሻ፤...) ማዘውተር
- በዓለም ያሉትን ሥጋዊ ወይም መንፈሳዊ ነገሮችን በአግባብ አለማየት።

የጋብቻ ፍቺ

- *ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ* “አዳም ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት የሚገባው ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ብዙ ሴቶችን ይፈጥርለት ነበር፤ በሥነ ፍጥረትም ሆነ ሰው በሚመራበት ትእዛዙ ሳይፋቱ እስከ መጨረሻው አብረው እንዲኖሩ አምላካችን እግዚአብሔር አዝዟል” በማለት ተናግሯል።

- ከፈረሰ ትዳር የተገኙ ወጣቶች ትዳራቸውን አጽንተው ከሚኖሩ ወላጆች ጋር አብረው ከሚኖሩ ወጣቶች ይልቅ ለወንጀልና ወንጀለኝነት መበራከት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

- ፍቺ ከጋብቻ በፊት ለሚፈጸም የእርስ በርስ መተዋወቅና ያለ አግባብም ለሚወለዱ ልጆች ምንጭ ነው። በተጨማሪነትም ፍቺ ለድህነት፤ ለአካላዊ ጤንነት መጓደል፤ ለአእምሮ መታወክ፤ ጸታን ዕድሜንና የገቢን ሁኔታም ከቁጥር ውስጥ ሳይለይ ለሚከሰተው የአደንዘዥ እጾች ሱሰኝነትም ያጋልጣል።

ትዳርን ከፍቺ ለመጠበቅ ምን እናድርግ?

- “እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።” *መዝ 127:1።* እንደተባለው ፍጹም ደስታና የምንሻው በሕይወታችን ሊነግስ የሚችለው እግዚአብሔር በትዳራችን፤ በቤታችን፤ በምናደርገው ነገር ሁሉ መካከል ካደረግነው ብቻ ነውና እግዚአብሔር የትዳሩ መሪ መሆኑ ዘወትር የተጠበቀ እንዲሆን እናድርግ። ባልና ሚስት አብረው ይጸልዩ፤ መጽሐፍ ቅዱስንም አብረው ያንብቡ። ።

- *በቆላስይስ 3:12-14።* “እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁየተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ። እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ። ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ። በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጻሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት።” በማለት እንደተጻፈው ራሳችንን በነዚህ የቅድስና መመሪያዎች የገዛን እንሁን።

- የትዳር አጋራችንን ቅዱስ ጳውሎስ በገለጣቸው በነዚህ በጎ ጎዳናዎች ለመውደድ የበቃን የሚያደርገን እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ እንወቅ። 1ኛ ቆሮ 7:27፤

- “እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል።” *ሚል 2:15* እንደተባለው ትዳራችንን ከማታለል የጸዳ እናድርገው።

ይቀጥላል...

መስበሐት
ለእግዚአብሔር።

በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

ኦርቶዶክሳዊ ጋብቻ - ክፍል 10

በጋብቻ ሕይወት የሚፈለግ መግባባት

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ
E-mail: kesisolomon3@gmail.com

ቦታ፡ **ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ**

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ሰኔ ፱ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

ግጭት

- የበሰሉ፣ ችሎታ አላቸው የሚባሉ ክርስቲያኖች ሳይቀሩ የተለያየ መጠን ባላቸው ግጭቶች ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ።
- የያዕቆብና የራሄል ሕይወት ለመግባባት እንቅፋት የሚሆነውን ግጭትን አስመልክቶ የሚያስተምረን ትምህርት አለ።

የግጭት ምክንያቶች

- የእንጀራ እናትነት - የእንጀራ ልጅነት… ዝምድና። ***ዘፍጥ 26:16-17፣ 29:23።***
  - ላባ አጋጣሚውን በመጠቀም ያዕቆብን ሰባት ዓመት ካገለገለው በኋላ አታልሎት ልያን እንዲያገባ አድርጎታል። ያዕቆብም ሰባት ተጨማሪ ዓመት ለማገልገልም ተገዷል።
  - ከእንጀራ እናት …ልጅነት… ዘመድ ጋር የሚኖር ጤናማ ያልሆነ ግኑኝነት ቋሚ የሆነ ግጭት ምንጭ ነው።
- የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ መለያየት። ***ዘፍጥ 31:19-34።***
  - ራሔል ጣዖትን ታመልክ ነበር። ቅዱስ መጽሐፍም ስለዚህ ያስጠነቅቀናል። ካል ቆሮ 6:14።
  - ለቃለ እግዚአብሔር እንግዳ ከሆነ/ች የትዳር አጋር ጋር መኖር በእግዚአብሔር ታምኖ ፈቃዱን እያደረጉ ለመኖር ተጨማሪ ጥንካሬን ይጠይቃል።
- ያልተወደድን ሆኖ ሲሰማን። ***ዘፍጥ 29:31-34፣ 30:20።***
  - ብቸኝነትና ያልተወደድን ሆኖ የሚሰሙን ስሜቶች ታላቅ ድህነቶች ናቸው።
  - በርካታ ተጋቢዎች ዓለም በሚፈልገው ቁሳዊ ነገር ስኬት አላቸው። ነገር ግን ለትዳር አጋራቸው ጥንቃቄ አንደሚያደርጉ ለማሳየት ግን ሕመም ይሰማቸዋል።
- ለመውለድ አለመቻል - መካንነት። ***ዘፍጥ 30:1-8።***
  - መካንነት በሰውነታችን ሊኖረን ከሚገባን የጎደለን ያለ መሆኑን የሚያሳስብ የሕመም ማስታወሻ ነው።
  - ራሔል በነበረችበት ዘመን የሴት ሀብትዋ ለባልዋ ልጆች መውለድ ነበር።
  - «ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው።» መዝ 127:3።
- የሩካቤ ችግር። ***ዘፍጥ 30:14-15።***

ግጭት

የግጭት መፍትሔዎች

- መተማመን፡፡ ***ኤፌ 4:25፡፡***
  - « ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ፡፡ »
  - ከማታለል በቀር መተማመንን የሚያቃልለው የለም፡፡
- ጊዜን መጠበቅ፡፡ ***ኤፌ 4:26፡፡***
  - “ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት፡፡”
  - ችግሮቹ እንደተፈጠሩ ወዲያው ካልሆነም ሳይፈጠሩ መፍትሔ መፈለግ፡፡
- ለነገሮች ተገቢ ግምት መስጠት፡፡ ***ኤፌ 4:29፡፡***
  - “ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ፥ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ፡፡”
  - ተራ ቃላቶችን እየተጠቀሙ መቀላለድ የትዳር አጋርን ሊጎዳ እንደሚችል መገመት ያስፈልጋል፡፡
  - « የለዘበች መልስ ቍጣን ትመልሳለች ሸካራ ቃል ግን ቍጣን ታስነሣለች፡፡» ***ምሳ 15:1፡፡***
- ይቅርታ፡፡ ***ኤፌ 4:31-32፡፡***
  - « መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ፡፡ እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡ »
  - ፍቅር ስህተቶችን አይከታተልም፡፡ « የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፡፡» ቀዳ ቆሮ 13፡5፡፡ ታዲያ በደልን የማንቆጥር መሆን እንዴት እንችላለን?
    1. አእምሮአችንን ለይቅርታ ማሰናዳት፡፡
    2. ትክክለኛ ምግባር ይዞ መገኘት፡፡ ኤፌ 4፡32፡፡
    3. እግዚአብሔር ከኛ አቅም በላይ የሆነውን እንዲሠራ መፍቀድ፡፡ ‹‹ እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ፡፡ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ፡፡ ›› ***ቆላ 3:13፡፡***
- **የሚከተሉትን መልካም ቃላቶች መጠቀም ለትዳር ሕይወት ማበብ ይረዳል፡፡ «አጥፍቻለሁ ይቅርታ አድርጊልኝ/ልኝ፣ እወድሃለሁ/እወድሻለሁ…፡፡»…**

በጋብቻ ሕይወት የሚፈለግ መግባባት

- **መግባባት በመናገር ወይም ሳይናገሩም መልእክትን ወይም መረጃን በሌላ ወገን የሚገኘው ሰው እንዲረዳ በማድረግ የሚከናወን ሂደት ነው።**
- **የመግባቢያ ግብአቶችም መናገር፣ መስማትና መረዳት ናቸው።**

ለመግባባት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች

- **ለመግባባት እንዳንችል ከሚያደርጉን ቁልፍ እንቅፋቶች መካከል አንዱ ሌሎች ሰዎች የተናገርነውን ሙሉ ለሙሉ እንደተረዱት አድርጎ ማሰብ ነው።**
- **አልፎ አልፎ የትዳር አጋራችን የተናገሩትን የተረዳን አድርገን ብናስብም አልፎ አልፎ ግን እኛ የሰማነው እርሱ/እርስዋ ፈጽሞ ያልተናገሩት ሆኖ ይገኛል።**
- **ከሰዎች ጋር ስንነጋገር ስድስት መልእክቶች ይተላለፋሉ፡-**
    1. **ልንል የፈለግነው**
    2. **በእርግጥ የተናገርነው**
    3. **ሌላው ሰው የሚሰማው**
    4. **ሌላው ሰው ሰማሁ ብሎ ያሰበው**
    5. **ሌላው ሰው እኛ ስለተናገርነው ያለው መረዳት**
    6. **ሌላኛው ሰው እኛ የተናገርነውን አስመልክቶ እንዴት እንደተናገረው የምናስበው ናቸው።**
- **መግባባት በጋብቻ ቁልፍ ነገር ነው።**

በጋብቻ ሕይወት የሚፈለግ መግባባት

- ራሳችንን መግባባት የሚጠበቅበት ሰው አድርገን እንውሰድና የመግባባት ችሎታችንን ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ከሦስቱ መልሶች አንዱ ላይ ከሥር በማስመር መልስ እንስጥ፡፡

1. ከትዳር አጋርዎ ጋር መግባባት ያስቸግርዎታል?
   አልፎ አልፎ፣ በጥቂቱ፣ እጅግ እየተቸገርኩ ነው
2. የትዳር አጋራችን የተናገርነውን (ምን ለማለት እንደፈለፈግን) ለመረዳት ይቸገራሉ?
   አልፎ አልፎ፣ በጥቂቱ፣ እጅግ ይቸገራሉ
3. የትዳር አጋራችን የመግባባት ችሎታችንን እንዴት ይገመግሙታል?
   በጣም ጥሩ፣ ደህና ነው፣ እጅግ አስቸጋሪ ነው በማለት

<u>አብዝቶ መሰማትና በጥቂቱ መናገር</u>

- ሰው ሁለት ጆሮ አንድ አንደበት ያለው መሆኑ አብዝቶ ከመናገር ይልቅ ለመስማት የተፈጠረ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡
- ወጣት ተጋቢዎች የትዳር ሕይወታቸውን መክፈል የሚገባቸውን ዋጋ በመክፈል የግኙኝነት መንገዳቸውን ግልጽ በማድረግ መጀመር ይኖርባቸዋል፡፡
- ይሁን እንጂ የግኙኝነት መሥመሮቹ የተዛቡ የመሆን ዕድል ይገትማቸዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ፡-
- ባል ወይም ሚስት በሕይወታቸው እየሆነ ባለው ጉዳይ ለመነጋገር ፈቃደና አለመሆናቸው ወይም
- በተጋቢዎቹ መካከል አንዱ ሲናገር ሌላው ያለማዳመጥ ችግር ያለባቸው መሆኑ ነው፡፡
- “ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፡፡” ያዕ 1:19
- ብዙዎቻችን ለመናገር የተዘጋጀን ብንሆንም ለመስማት ግን ፍላጎት አጥተን የምንገኝ ነን፡፡
- ውጤታማ ለሆነ የትዳር ሕይወት ቁልፉ ነገር ግን የትዳር አጋርን መስማት መቻል ነው፡፡ ይህም በራስ የመወሰንን በውሳኔውም የትዳር አጋርን አንድ ተፈላጊ የሕይወት አካል አድርጎ ለመቁጠር ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

በጋብቻ ሕይወት የሚፈለግ መግባባት

ብርቱ የመሰማት ችሎታ

- ጤናማ መግባባት ሊኖር የሚችለው በትክክል መደማመጥ ወይም መስማት ባለበት ቦታ ብቻ ነው።
- በየመካከሉ መስማታችንን የሚያረጋግጥ ‹‹አዎ...›› የሚል ምልክት ለመስጠት ከመናገር በቀር አንደበትን ገዝቶ አፍን ዘግቶ ማዳመጥ በጋብቻ ውስጥ የሚፈለግ ለመግባባት የሚያስችል ችሎታ ነው።
- እስኪ ስለ ራሳችን የመግባባት ልምድ እናስብ፡-
    1. የትዳር አጋራችንን በርግጥ እንሰማለን?
    2. በትዳር አጋራችንን ከተነገረን ምን ያህሉን እንሰማለን?

የቃላት ክብደት

- ቃላት ሰውን ሊጎዱ ይችላሉ።
- “ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ፥ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ።” *ኤፌ 4:29።*
- የትዳር አጋራችንን የሕይወት ልምድ በመልካም ቃሎች መገንባት የመቻላችንን ያህል ጥቅም የሌላቸው ሆነው እንዲሰማቸውና ተገልለው በመኖር ወደ ሞት ለማምራታቸውም ተጠያቂ ልንሆን እንችላለን።
- “ነፍሴን የምትነዘንዙ፥ በቃልስ የምታደቅቁኝ እስከ መቼ ነው?” *ኢዮብ 19:2።*

ከመናገራችንን በፊት ማሰብ

- ባል ወይም ሚስት የተሰማቸውን ዌወም ያሰቡትን ዝም ብለው የሚያፈነዱ መሆን የለባቸውም።
- “በቃሉ የሚቸኩለውን ሰው ብታይ፥ ከእርሱ ይልቅ ለሰነፍ ተስፋ አለው።” *ምሳሌ 29:20።*
- ክርስቲያን የሆኑ ተጋቢዎች መንፈስቅዱስ ባደላቸው ጥንካሬ ለጊዜውና ለሁኔታው ተስማሚ የሆኑ ቃላትን መምረጥ ይችላሉ።

ትክክለኛውን ጊዜ መጠበቅ

- መጥፎ መርዶ ስናረዳ፣ ከበድ ያሉ ነገሮችንን ከትዳር አጋራችን ጋር ስንነጋገር ፍቅር መሪያችን ይሁን።
- “የወርቅ እንኮይ በብር ዓሕል ላይ የጊዜው ቃል እንዲሁ ነው።” *ምሳሌ 25:11።*
- “ሰው በአፉ መልስ ደስ ይለዋል ቃልም በጊዜው ምንኛ መልካም ነው!” *ምሳሌ 15:23።*

በጋብቻ ሕይወት የሚፈለግ መግባባት

አንደበትን መግዛት

- “ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ብዙዎቹ አስተማሪዎች አይሁኑ፥ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና። ሁላችን በብዙ ነገር እንሰናከላለንና፤ በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ሥጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው። እነሆ፥ ፈረሶች ይታዘዙልን ዘንድ ልጓም በአፋቸው ውስጥ እናገባለን፥ ሥጋቸውንም ሁሉ እንመራለን። እነሆ፥ መርከቦች ደግሞ ይህን ያህል ታላቅ ቢሆኑ በዐውሎ ነፋስም ቢነዱ፥ የመሪ ፈቃድ ወደሚወደው ስፍራ እጅግ ታናሽ በሆነ መቅዘፊያ ይመራሉ። እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል። እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል። አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል። የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል፥ ደግሞ ተገርቶአል፤ ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፋት ነው። በእርሱ ጌታንና አብን እንባርካለን፤ በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን፤ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም። ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን? ወንድሞቼ ሆይ፥ በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን? ከጨው ውኃም ጣፋጭ ውኃ አይወጣም።” **ያዕ 3፡1-12።**
- **በቁጥር 3-4 እንደጠጠቀሰው ባልና ሚስት ትዳራቸውን ወደ ሚፈልጉበት አቅጣጫ ሊመሩት ይችላሉ። ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ትዳራቸው የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት እንዲሆን አንደበታቸውን መግዛት ይጠበቅባቸዋል።**
- **በቁጥር 5 እንደተጠቀሰው ትዳር በባል/በሚስት አስተያየት፣ የማያቋርጥ ወቀሳ፣ ነቀፋ ወይም ስድብ በማይጠገንበት መልኩ ሊሰበር ይችላል።**

ስለዚህ ተጋቢዎች ክፋትን የተሞላ፣ እረፍት የሌለው መርዛማ ሳይሆን በምስጋናና በበረከት የተሞላ በማድረግ አንደበትን ለመግራት ጠንክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

አንደበትን መግዛት

- “ባልም ሆነ ሚስት ከራሳቸው ይልቅ ለትዳር አጋራቸው ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጡ ከሆነ እርስ በርሳቸው ለመግባባት ታላቅ እመርታን ያደርጋሉ።
- **የትዳር አጋርን ለመረዳት ጥረት ማድረግ የራስን ዋጋና ክብር ከፍ ያደርጋል። ስለዚህ ስንናገር የትዳር አጋራችን የበለጠ ሊረዱ በሚችሉበት ይህን በመሰለ መንገድ እንናገር።**

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org

መስብሐት ለእግዚአብሔር።